PAARTII BADHAADHIINAA
ብልጽግና ፓርቲ
PROSPERITY PARTY

# የብልጽግና ፓርቲ የአባላትና የአመራር አካላት አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር

# ጊዜያዊ መመሪያ

የካቲት/2012

አዲስ አበባ

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

መግቢያ ........ 3
ክፍል አንድ ........ 4
የፌዴራልና የክልል አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር ........ 4
ክፍል ሁለት ........ 11
የዞን/የልዩ ወረዳ አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር ........ 11
ክፍል ሶስት ........ 15
የወረዳ አመራር አደረጃጀት ተልዕኮና አሰራር ........ 15
ክፍል አራት ........ 19
የአዲስ አበባ፣ ድሬደዋ እና ለክልል ተጠሪ የሆኑ ከተሞች አመራር አደረጃጀት ተልዕኮና አሰራር ........ 19
ክፍል አምስት ........ 29
ለዞን/ለወረዳ/ልዩ ወረዳ ተጠሪ የሆኑ ከተሞች አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር ........ 29
ክፍል ስድስት ........ 33
የቀበሌ አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር ........ 33
ክፍል ሰባት ........ 36
በየደረጃው የሚኖር የፓርቲ ኮንፈረንስ ውክልና፣ ........ 36
ክፍል ስምንት ........ 37
የመሰረታዊ ድርጅትና የሕዋሳት አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር ........ 37

# የብልጽግና ፓርቲ የአባላትና የአመራር አካላት አደረጃጀት፤ ተልዕኮና አሰራር ጊዜያዊ መመሪያ

## መግቢያ

የብልፅግና ፓርቲ የውህደት ውጤት ሆኖ ሲመሰረት ያፀደቀውን መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በማድረግ በዝርዝር ጥናት ላይ ተመስርቶ የአደረጃጀት መመሪያ የመቅረጽ አስፈላጊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ እስከሚሆን ድረስ በቀደመው አሰራር መቀጠል ስለማይቻል የዚህን ጊዜያዊ መመሪያ መውጣት አስፈላጊ አድርጎታል፡፡ ከዚህ በመነሳት የብልፅግና ፓርቲ ተልዕኮው እና አሰራሩ ወጥነት እንዲኖረው እና አሁን ከደረስንበት የዕድገት ደረጃ በመነሳት በየደረጃ ያለውን የአመራር አካላት አደረጃጀት፤ ተልዕኮ እና አሰራር ለመወሰን የሚያስችል የተሟላ መመሪያ እስኪዘጋጅ ጊዜያዊ መመሪያ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ማዋል አሰፈላጊ በመሆኑ፤

ከዚህ በፊት በተለያየ መዋቅር ተበታተነው የነበሩትን አደረጃጀቶች ሰብሰብ በማድረግና ሁሉንም በሚያካትት እንዲሁም የፓርቲያችን ተልዕኮ እና የሀገራችን ብልጽግና ለማረጋገጥ የሚያስችል የፓርቲ አደረጃጀት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል መነሻ መመሪያ በማስፈለጉ፤

መመሪያውን ከፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ጀምሮ እሰከ ቀበሌ ድረስ ያለው አደረጃጀት እንዴት ተሳስሮ እና ተናቦ መሄድ እንዳለበት የሚያሳይና በጋራ በመደጋገፍ የለውጥ ተግባራት አሰተማማኝ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ብሎም የታሰበውን ሀገራዊ ብልጽግና ዳር ለማድረስ በሚያግዝ መልኩ ማዘጋጀት በመታመኑ፤

በየደረጃው ያለው አመራር እና አባል በቀላሉ ለመጠቀም እንዲያስችለው በማሰብ የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ በመከተል ይህ ጊዜያዊ መመሪያ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

# ክፍል አንድ

## የፌዴራልና የክልል አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር

## አንቀጽ 1፡ የፌዴራል አመራር አደረጃጀት፣

የብልጽግና ፓርቲ መተዳደሪ ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔዎች ለማስፈፀም ፌዴራል አመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የፌደራል ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ
2. የፌዴራል ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ

## አንቀጽ 2፡ የፌደራል ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት

የፌዴራል አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የብልጽግና ፓርቲ ፕሬዝዳንት ........................................................ሰብሳቢ
2. የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዝዳንቶች ..........................................አባል
3. የፌደራል ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ..........................................................አባል
4. የፖለቲካ ዘርፍ ሃላፊ ..................................................................................አባል
5. የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ................................................................... አባል፣
6. የፓርቲዎችና ሲቪክ ማህበራት ክትትል ዘርፍ ኃላፊ ..........................አባል
7. የጥናትና ምርምር ዘርፍ ኃላፊ ..........................................................አባል
8. የህዝብና አለም አቀፍ ግንኙነት ዘርፍ ኃላፊ .................................... አባል፣

## አንቀጽ 3፡ የፌደራል ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፣

1. ከፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት የፓርቲውን የፖለቲካ እና የድርጅት ስራዎች በበላይነት ያስተባብራሉ፣
2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የማዕከላዊ ኮሚቴ ያወጣውን እቅድ አፈፃፀም ስራን ተከታትሎ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣
3. የፓርቲና የመንግስት ስራዎች ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣

4. በፓርቲው የሚካሄዱ የፓርቲና የመንግስት የማድረግ አቅምን ለማሳደግ የሚሰጡ ስልጠናዎችን ያቅዳል፣ ይመራል ይከታተላል፣
5. በየደረጃው ያሉትን የፓርቲና የመንግስት አመራር አካላትን ፖለቲካዊ ብቃት በመገንባት ተልዕኳቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ የማብቃት ስራ ይሰራል፣
6. በፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የወጡ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ እንዲፈፀም ድጋፍ ይሰጣል፣
7. የፓርቲውን አመራርና አባል፣ የህዝብ፣ የተፎካካሪ ኃይሎችን ሁኔታ በዝርዝር በማወቅ እየገመገመ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፣
8. ስለ ስራው ክንውን ለፓርቲው ስራ አስፈፃሚ ሪፖርት ያቀርባል፣
9. ጠንካራ የክትትና ድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት ስራን ይመራል፣
10. ተጠሪነቱ ለፓርቲው ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 4. የፌደራል ብልጽግና ፓርቲ አስተባባሪ አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ በአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 5፡ የፌደራል ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የፌደራል ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1. የፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ..................................................................ሰብሳቢ
2. የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ...............................................................ም/ሰብሳቢ
3. የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ............................................................... አባል፣
4. የፓርቲዎና ሲቪክ ማህበራት ክትትል ዘርፍ ኃላፊ .............................አባል
5. የህዝብና አለም አቀፍ ግንኙነት ዘርፍ ኃላፊ ......................................አባል
6. የጥናት ምርምር ዘርፍ ኃላፊ ........................................................... አባል፣
7. በፓርቲ ጽ/ቤት የወጣቶችና ሴቶች ሊግ ሰብሳቢዎች ያለድምፅ ........ አባል፣

8. የፓርቲው ጽ/ቤት ኃላፊ እንደየ ሁኔታውና አስፈላጊነቱ በአመራር ኮሚቴዉ እያስወሰነ ሌሎች ኃላፊዎችን የኮሚቴው አባል ማድረግ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 6፡ የፌደራል ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፣

1. የፓርቲው ጽ/ቤት በመተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የብልጽግና ፓርቲ የፖለቲካ፣ የአደረጃትና የህዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. የፓርቲውን አመታዊ መነሻ እቅድ በማዘጋጀት በማዕከላዊ ኮሚቴው ሲፀድቅ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፡፡ ያሰማራል በስራው ሂደትም ተከታትሎ ይደግፋል፡፡ ስለአፈፃፀሙም ለፓርቲው ፕሬዝዳንትና ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሪፖርት በማዘጋጀት ያቀርባል፣
3. በፓርቲው የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር የስልጠና ስራ ያጠናል፡፡ ያቅዳል፣ ያደራጃል ስልጠናውም እንዲካሄድ ያደርጋ፡፡
4. የፓርቲው የአሰራርና የአደረጀቃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል ችግሮችን ይለያል፣ መፍትሂ አቅጣጫ ይቀይሳል፣ ለውጡ ቀጣይነት እንዲኖረው አበክሮ ይሰራል፡፡
5. የፓርቲውን ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የስራ አፈፃፀም እና እቅዶ በሚዲያና በህዝብ ግንኙነት መሳሪያዎች ለህዝብ ያስተዋውቃሉ፡፡
6. ፓርቲው አባላት ማህደር መረጃ፣ የፓርቲ ገንዘብ፣ ንብረትና ሰነዶች በበላይነት ያስተዳድራሉ፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፣
7. በፓርቲው የሰው ሀይል አስተዳደር መመሪያ መሰረት የጽ/ቤቱን ሰራተኞች ይቀጥራል ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣
8. የፓርቲ አመራርና አባል፣ የክልሉ ሕዝብ የተፎካካሪዎች ሁኔታን በየጊዜው እየተከታተለ ተገቢውን አቅጣጫ እየሰጠ ይሄዳል፣
9. የአመራር የስነ-ምግባርና የመፈፀም ብቃት በማዳበር የአባሉን የተደራጀ እንቅስቃሴ የሚመራ ጠንካራ አመራር መፍጠር በበቂ ቁጥር እንዲፈጠር ያቅዳል፣ ይፈፅማል፡፡
10. የክልል አመራርን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣

11. የሚከተለውን የክትትልና ድጋፍ ሥራ ያከናውናል፣ ሳምንታዊ አጭር የስራ ግምገማ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ ለሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ያደርጋል፡፡ በየሩብ አመቱ ከክልል ፓርቲ ጽ/ቤቶች ጋር መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል በየስድስት ወሩ ክልሎችን፣ ዞኖችንና ወረዳዎችን ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ በአካል በመውረድ ያያል፣ ይገመግማል ድጋፍ ይሰጣል።
12. በብልፅግና ልሳንና በራሪ ጽሑፎች እንዲሁም መጽሔት ለሚካሄደው የአባላት ግንባታ አጀንዳዎችን በመቅረጽ ያስተላልፋል፡፡
13. የጽ/ቤቱን በጀት በማዘጋጀትና በፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ሲፀድቅ በአግባቡ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
14. ተጠሪነቱ ለፓርቲው ፕሬዚዳንት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 7፡ የፌደራል ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባዔው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምፅ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካል ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 8. የክልል አመራር አካላት አደረጃጀት፣

የብልፅግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል አመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የክልል ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ
2. የክልል ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ

## አንቀጽ 9. የክልል ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት

የክልል አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ........................................................ ሰብሳቢ
2. የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር........................................... አባል

3. በክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የተመደቡ አመራሮች...... አባላት
4. የክልል ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ........................................................ ም/ሰብሳቢ
5. የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ................................................................. አባል
6. የአደረጃት ዘርፍ ኃላፊ ............................................................... አባል

## አንቀጽ 10. የክልል ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. ከፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የክልሉን የፖለቲካ እና የድርጅት ሥራዎች በበላይነት ያስተባብራሉ፣
2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የማዕከላዊ ኮሚቴ ያወጣውን ዕቅድ አፈፃፀም ስራን ተከታትሎ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣
3. የፓርቲና የመንግስት ስራዎች ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣
4. በክልሉ የሚካሄዱ የፓርቲና የመንግስት የማድረግ አቅምን ለማሳደግ የሚሰጡ ስልጠናዎችን ያቅዳል፣ ይመራል ይከታተላል፣
5. በክልሉ በየደረጃው ያሉትን የፓርቲና የመንግስት አመራር አካላትን ፖለቲካዊ ብቃት በመገንባት ተልዕኮአቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ የማብቃት ስራ ይሰራል፣
6. በፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የወጡ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ እንዲፈፀም ድጋፍ ይሰጣል፣
7. የክልሉን የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ምደባ የውሳኔ ሐሳብ ቀጥሎ ላለው የፓርቲ ጽ/ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ያሰማራል፣ እንዲሁም የክልሉን ቀሪ አመራሮች፣ የዞን፣ ለክልል ተጠሪ የሆኑ ከተሞችና ልዩ ወረዳዎች አመራር ምደባ ያፀድቃል፣
8. በክልሉ አጠቃላይ የፓርቲውን አመራርና አባል፣ የሕዝብ፣ የተፎካካሪ ሃይሎችን ሁኔታ በዝርዝር በማወቅ እየገመገመ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፣፡፡
9. ስለ ሥራው ክንውን ለፓርቲው ስራ አስፈፃሚና ለፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡
10. ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርአት በመዘርጋት ስራን ይመራል፣
11. ተጠሪነቱ ለፓርቲው ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 11. የክልል ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡
2. ምልዓተ ጉባዔው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 12. የክልል ብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት

የክልል ብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1. የፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ………………………………… ሰብሳቢ
2. የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ………………………………… ም/ሰብሳቢ
3. የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ……………….……………. አባል
4. የህዝብ ግንኙነት ዘርፍ ኃላፊ …………………………. አባል
5. የጥናትና ምርምር ዘርፍ ኃላፊ ……………………….. አባል
6. በፓርቲ ጽ/ቤት የወጣቶችና ሴቶች ሊግ ሰብሳቢዎች ያለድምፅ አባል
7. የክልሉ የፓርቲው ጽ/ቤት ኃላፊ እንደየ ክልሉ ሁኔታና አስፈላጊነት በአመራር ኮሚቴዉ እያስወሰነ ሌሎች ኃላፊዎችን የኮሚቴው አባል ማድረግ ይችላል፣

## አንቀጽ 13. የክልል ብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የፓርቲው ጽ/ቤት በመተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የክልሉ የፖለቲካዊ፣ የአደረጃጀትና የሕዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ከዋና ፓርቲ ጽ/ቤት የሚወርዱ ዕቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ክልል ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፣ ያሰማራል በስራው ሂደትም ተከታትሎ ይደግፋል፡፡
3. የአባላት የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራን በተቀመጠው አቅጣጫ እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው

እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ ጠንካራ የሕዋስና የመሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፡፡

4. በፓርቲው የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር የስልጠና ስራ ያጠናል፣ ያቅዳል፣ ያደራጃል ስልጠናውም እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡
5. የፓርቲ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል ችግሮችን ይለያል፣ የመፍትሔ አቅጣጫ ይቀይሳል፣ ለውጡ ቀጣይነት እንዲኖረው አበክሮ ይሰራል፣
6. በፓርቲው ዋና ጽ/ቤት በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የፓርቲውን ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የሥራ አፈፃፀም እና ዕቅዶች በሚዲያና በሕዝብ ግንኙነት መሳሪያዎች ለሕዝብ ያስተዋውቃሉ፣
7. በክልሉ የሚገኙ የአባላት ማህደር መረጃ፣ የፓርቲ ገንዘብ፣ ንብረትና ሰነዶች በበላይነት ያስተዳድራሉ፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፣
8. በፓርቲው የሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሰረት የጽ/ቤቱን ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣
9. የየፓርቲ አመራርና አባል፣ የክልሉ የሕዝብ፣ የተፎካካሪዎች ሁኔታን በየጊዜው እየተከታተለ ተገቢውን አቅጣጫ እየሰጠ ይሄዳል፡፡
10. የአመራር የስነ-ምግባርና የመፈፀም ብቃት በማዳበር የአባሉን የተደራጀ እንቅስቃሴ የሚመራ ጠንካራ አመራር መፍጠር በበቂ ቁጥር እንዲፈጠር ያቅዳል፣ ይፈፅማል፡፡
11. የዞን የከተማና የወረዳ አመራርን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ መስጠት።
12. የሚከተለውን የክትትልና ድጋፍ ሥራ ያከናውናል፡- ሳምንታዊ አጭር የስራ ግምገማ፣ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ ለሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ይደረጋል፡፡ በየወሩ በክልሉ ካሉት ዞኖችና ለክልል ተጠሪ የሆኑ ከተሞችን በየ6 ወሩ ወረዳዎችን ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ በአካል በመውረድ ያያል፣ ይገመግማል ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ለብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት በ2 ሳምንት የስራ ኢንፎርሜሽን ልውውጥ ያደርጋል፣ በወር አጭር የፅሑፍ ሪፖርት፣ በየ3 ወሩ አጠቃላይ የስራ ሪፖርትና የጋራ መድረክ ይኖረዋል፡፡

13.በብልፅግና ልሳንና በራሪ ጽሑፎች እንዲሁም መፅሔት ለሚካሄደው የአባላት ግንባታ አጀንዳዎችን በመቅረጽ ያስተላልፋል፡፡

14.የጽ/ቤቱን በጀት በማዘጋጀትና በፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ሲፀድቅ በአግባቡ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

15.ተጠሪነቱ ለክልሉ ፓርቲው አስተባባሪ ኮሚቴና ለዋና ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 14፡ የክልል ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር፣

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የዞን/የልዩ ወረዳ አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር

## አንቀጽ 15፡ የዞን፣ የልዩ ወረዳ አመራር አካላት አደረጃጀት

የዞን/ልዩ ወረዳ አመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ፣
2. የፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ

## አንቀፅ 16፡ የዞን/ልዩ ወረዳ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የዞን/ልዩ ወረዳ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣

1. አስተዳዳሪ ...........................................................................................ሰብሳቢ
2. ም/አስተዳዳሪ .......................................................................................አባል
3. የፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ..................................................................ም/ሰብሳቢ
4. የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ .....................................................................አባል

5. የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ..................................................................አባል

## አንቀጽ 17፡ የዞን/ልዩ ወረዳ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፣

1. ከክልሉ አስተባባሪ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የዞኑን፣ ልዩ ወረዳ የፖለቲካ ስራና የመንግስት ስራዎች የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ይከታተላል፤ ይመራል፣
2. የፓርቲና የመንግስት ስራዎች ተቀናጅው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣ ይገመግማል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
3. በዞኑም፣ በልዩ ወረዳ ሆነ ከዛ ውጪ የተገኙ መልካም ልምዶችን በመቀመር በዞኑ/በልዩ ወረዳው ውስጥ የማስፋት ስራ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣
4. የሚካሄዱ የፓርቲና የመንግስት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይከታተላል፤ ይመራል፣ እንዲሁም በዞኑ፣ ልዩ ወረዳ ያሉትን የፓርቲ አመራር አካላትን በቅርበት ይደግፋል፣
5. በየደረጃው ያሉትን የፓርቲና የመንግስት አመራር አካላትን ፖለቲካዊ ብቃት በመገንባት ተልእኳቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ ስራ ይሰራል፣
6. የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴና ካቢኔ አባላት ምደባ የውሳኔ ሃሳብ ቀጥሎ ላለው የፓርቲ ጽ/ቤት ያቀርባሉ፡፡ ሲጸድቅ ያሰማራሉ፣ ለዞን ተጠሪ የሆኑ ከተሞችና ወረዳዎች፣ ለልዩ ወረዳ ተጠሪ የሆኑ ቀበሌዎች፣ ከተሞች አስተባባሪና ካቢኔ አባላት ያፀድቃል፣
7. ከፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የወጡ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በዞኑ/በልዩ ወረዳ በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ያስፈፅማል፣ ይፈፅማል፣
8. በዞኑ/ልዩ ወረዳ የመዋቅር፣ የህዝብ፣ የተፎካካሪ ፓርቲና አፍራሽ ኃይሎች ሁኔታን በዝርዝር በማወቅ እየገመገመ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፡፡
9. ተጠሪነቱ ለክልሉ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 18፡ የዞን/ልዩ ወረዳ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡

3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 19፡ የዞን/ልዩ ወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የዞን/ልዩ ወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ...........................................................................ሰብሳቢ
2. የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ .....................................................................ም/ሰብሳቢ
3. የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ .........................................................................አባል
4. የፓርቲ ህዝብ ግንኙነት ዘርፍ ኃላፊ ......................................................አባል
5. የወጣቶችና ሴቶች ሊግ ሰብሳዎች ያለድምጽ .........................................አባል
6. የፓርቲው ጽ/ቤት ኃላፊ እንደአስፈላጊነቱ በአመራር ኮሚቴዉ እያስወሰነ ሌሎች የስራ ኃላፊዎችን ሊጨምር ይችላል፡፡

## አንቀጽ 20፡ የዞን/ልዩ ወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የፓርቲው ጽ/ቤት በመተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የዞን/ልዩ ወረዳ የፖለቲካ፣ የአደረጃጀትና የህዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ከክልሉ ፓርቲ ጽ/ቤት የሚወርዱ እቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ የዞን፣ ልዩ ወረዳ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚውን አካል ኦረንቴሽን ሰጥቶ ያሰማራል፣ የስራውን አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይመራል፣
3. በየደረጃው ያለው የፓርቲ አደረጃጀት አመራርና አባላት በስራቸው ግምባር ቀደም እንዲሆኑ ፖለቲካዊ ግንዛቤያቸው እንዲዳብር ያደርጋል፣
4. የአባላት የእለት ተእለት ግንባታ ስራን በተቀመጠው አቅጣጫ እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ ጠንካራ የህዋስና መሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ይመራል፣

5. በዞኑ/ልዩ ወረዳ የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር ስልጠና፣ ሴሚናር፣ የመ/ድርጅቶች ኮንፈረንስ ያስተባብራል፣ ይመራል፣
6. የፓርቲው የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በዞኑ/ልዩ ወረዳ በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል ያስፈፅማል፣
7. በዞኑ/ልዩ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ የአባላት ማህደር፣ መረጃ የፓርቲ ሰነዶች የፓርቲውን ገንዘብና ንብረት በበላይነት ያስተዳድራል፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
8. የዞኑ፣ ልዩ ወረዳ ህዝብ፣ የተፎካካሪና አፍራሽ ኃይሎች ሁኔታን በየጊዜው እየተከታተለ ተገቢው የማስተካከያ አቅጣጫ እየሰጠ ይሄዳል፣
9. የአመራርን የስነ ምግባርና የመፈፀም ብቃት በማዳበር የአባሉን የተደራጀ አህዳዊ እንቅስቃሴ የሚመራ ጠንካራ አመራር ስራ ይደግፋል፣ ብቃት ያለው አመራር በበቂ ቁጥር እንዲፈጠሩ አቅዶ ይሰራል፣
10. በልሳናትና በራሪ ጽሁፎች እንዲሁም በብልጽግና መጽሄት ላይ ለሚካሄደው የአባላት ግንባታ ከክልል ፓርቲ ጽ/ቤት የሚተላለፋትን ከዞኑ/ልዩ ወረዳ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ያደርጋል፣
11. ለክልል ፓርቲ ጽ/ቤት በ2 ሳምንት የኢንፎርሜሽን ልውውጥ ያደርጋል፣ በወር አጭር የጽሁፍ ሪፖርት፣ በየ3 ወሩ አጠቃላይ የስራ ሪፖርትና የጋራ መድረክ ይኖረዋል ለዚህም የግምገማ እና ሂስ ግለሂስ ተደርጎ ማህደር ይሞላል፡፡
12. ተጠሪነቱ ለክልል አስተባባሪ ኮሚቴና ለክልል ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ይሆናል።

## አንቀጽ 21. የዞን፣ ልዩ ወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር፣

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡
4. የወረዳ/የከተማ/ቀበሌ አመራርን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፡፡

ሀ) በየሩብ አመቱ ከወረዳ/ከተማ/ቀበሌ ጽ/ቤት አመራር ጋር የስራ ግምገማ ያደርጋል

ለ) በየወሩ ወረዳዎች/ቀበሌዎች ያሉበት የአፈፃፀም ደረጃ የጽሁፍ ሪፖርት ተቀብሎ ተገቢውን ግብረ መልስና ድጋፍ ይሰጣል፡፡

ሐ) በየሳምንቱ ከወረዳዎች/ቀበሌዎች ጋር በስልክ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ኢንፎርሜሽን ይቀበላል፡፡

መ) አመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማና የቀጣይ አመት እቅድ ለወረዳ/ከተማ/ቀበሌ ፓርቲ አመራር ኦረንቴሽን ይሰጣል፡፡ በየ3 ወሩ ደግሞ ከጠንካራ፣ መካከለኛና ደካማ ወረዳዎች/ቀበሌዎች ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ በአካል ይገመግል የድጋፍ አቅጣጫንም ያስቀምጣል፡፡

# ክፍል ሶስት

# የወረዳ አመራር አደረጃጀት ተልዕኮና አሰራር

## አንቀጽ 22. የወረዳ አመራር አካላት አደረጃጀት፣

የወረዳ አመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

የዞን/ልዩ ወረዳ አመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ፣
2. የፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ

## አንቀፅ 23. የወረዳ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የወረዳ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣

1. አስተዳዳሪ ..................................................................................ሰብሳቢ
2. ም/አስተዳዳሪ ..............................................................................አባል
3. የፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ..................................................................ም/ሰብሳቢ
4. የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ....................................................................አባል
5. የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ...............................................................አባል

## አንቀጽ 23. የወረዳ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. ከዞን አስተባባሪ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የወረዳውን የፖለቲካ ስራና የመንግስት ስራዎች የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ይከታተላል፤ ይመራል፣
2. የፓርቲና የመንግስት ስራዎች ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣
3. በወረዳው የሚካሄዱ የፓርቲና የመንግስት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይከታተላል፣ ይመራል እንዲሁም በስሩ ያሉትን የቀበሌ አመራር አካላትን በቅርብ ይደግፋል፡፡
4. የፓርቲና የመንግስት አመራር አካላትን ፖለቲካዊ ብቃት በመገንባት ተልዕኳቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ ስራ ይሰራል፡፡
5. የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴና ካቢኔ አባላት ምደባ የውሳኔ ሀሳብ ቀጥሎ ላለው የፓርቲ ጽ/ቤት ያቀርባሉ፣ ሲጸድቅ ያሰማራሉ፣ የቀበሌ አስተባባሪና የካቢኔ አባላት ምደባ ያከናውናሉ፡፡
6. ከፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የወጡ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ያስፈፅማል፣ ይፈፅማል፡፡
7. በወረዳው የመዋቅር የህዝብ፣ የተፎካካሪ ፓርቲዎችና አፍራሽ ኃይሎች ሁኔታን በዝርዝር በማወቅ እየገመገመ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፡፡
8. የፓርቲው የአሰራርና አደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በወረዳው ውስጥ በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይገመግማል፡፡
9. ተጠሪነቱ ለዞን ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴና ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 25. የወረዳ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡ በ5 ቀናት ውስጥ በመንግስትና በፓርቲ መስክ የተከናወኑ ስራዎችን አጠር ያለ ግምገማ ያደርጋል፡፡ በሚቀጥሉት 15 ቀናት ውስጥ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ላይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 26. የወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ አባላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ........................................................................ሰብሳቢ
2. የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ..................................................................ም/ሰብሳቢ
3. የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ....................................................................አባል
4. በፓርቲ ጽ/ቤት ቋሚ ሆነው የሚሰሩ የወጣቶችና ሴቶች ሊግ ኃላፊዎች ያለድምጽ ...........................................................................................................አባል
5. የፓርቲው ጽ/ቤት ኃላፊ እንደአስፈላጊነቱ በአመራር ኮሚቴዉ እያስወሰነ ሌሎች የስራ ኃላፊዎችን ሊጨምር ይችላል፡፡

## አንቀጽ 27. የወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የፓርቲው ጽ/ቤት በመተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የወረዳ የፖለቲካ፣ የአደረጃጀትና የህዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ከዞን ፓርቲ ጽ/ቤት የሚወርዱ እቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚውን አካል ኦረንቴሽን ሰጥቶ ያሰማራል፣ የስራውን አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይመራል፣
3. የፓርቲ አደረጃጀት አመራርና አባላት በስራቸው ግምባር ቀደም እንዲሆኑ ፖለቲካዊ ግንዛቤያቸው እንዲዳብር ያደርጋል፣
4. በወረዳው የሚካሄደውን የልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራዎች ከመተግበር አኳያ ያሉ መልካም ልምዶችን እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡
5. የአባላት የእለት ተእለት ግንባታ ስራን በተቀመጠው አቅጣጫ እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ ጠንካራ የህዋስና መሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ይመራል፣
6. በወረዳ የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር ስልጠና፣ ሴሚናር፣ የመ/ድርጅቶች ኮንፈረንስ ያስተባብራል፣ ይመራል፣

7. የፓርቲው የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል ያስፈፅማል፣ ይፈጽማል፣
8. በወረዳ ውስጥ በሚገኙ የአባላት ማህደር፣ መረጃ የፓርቲ ሰነዶች የፓርቲውን ገንዘብና ንብረት በበላይነት ያስተዳድራል፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
9. የወረዳው መዋቅር ህዝብ፣ የተፎካካሪና አፍራሽ ኃይሎች ሁኔታን በየጊዜው እየተከታተለ ተገቢው የማስተካከያ አቅጣጫ እየሰጠ ይሄዳል፣
10. የአመራርን የስነ ምግባርና የመፈፀም ብቃት በማዳበር የአባሉን የተደራጀ አህዳዊ እንቅስቃሴ የሚመራ ጠንካራ አመራር ስራ ይደግፋል፣ ብቃት ያለው አመራር በበቂ ቁጥር እንዲፈጠሩ አቅዶ ይሰራል፣
11. በልሳናትና በራሪ ጽሁፎች እንዲሁም በብልጽግና መጽሄት ላይ ለሚካሄደው የአባላት ግንባታ ከዞን ፓርቲ ጽ/ቤት የሚተላለፉትን ከወረዳ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ያደርጋል፣
12. ተጠሪነቱ ለዞን አስተባባሪ ኮሚቴና ለክልል ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 28. የወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## የአዲስ አበባ፣ ድሬደዋ እና ለክልል ተጠሪ የሆኑ ከተሞች አመራር አደረጃጀት ተልዕኮና አሰራር

### አንቀጽ 29፡ አመራር አካላት

የከተማ/አስተዳደሩ አመራር አካላት የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የከተማ/የአስተዳደሩ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ፣
2. የከተማ/የአስተዳደሩ ፓርቲ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ

### አንቀጽ 30፡ የከተማ/የአስተዳደሩ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት

የከተማ/የአስተዳደሩ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1. ከንቲባ ........................................................................................ሰብሳቢ
2. ምክትል ከንቲባ ..............................................................................አባል
3. የብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ....................................................ም/ሰብሳቢ
4. የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ ......................................................................አባል
5. የአደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ ......................................................አባል ይሆናሉ፡፡

### አንቀጽ 31. የከተማ/የአስተዳደሩ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. ከበላይ አካል በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የከተማውን የፖለቲካ ስራና የመንግስት ስራዎች የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ይከታተላል ይመራል፣
2. የከተማ/አስተዳደሩና የበላይ አካል አጠቃላይ አመራር ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በተሟላ መንገድ በስራ ላይ እንዲውሉ መከታተል፣ ማስፈፀም፣ መፈፀም
3. የፓርቲና የመንግስት ስራዎች ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣ ይገመግማል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
4. በከተማው/አስተዳደሩ የሚገኙ የመሰረታዊ ድርጅትና የህዋስ አመራር በስሩ ያሉትን አባላት አደራጅቶ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል አቅም እንዲኖረው ማስቻል፣
5. የከተማው/አስተዳደሩ እንዲሁም የመሰረታዊ ድርጅትና የህዋስ አመራሩ መልካም ልምዶችን በማስፋት የአቅም ግንባታ ስራ ይሰራል፡፡

6. የከተማውን/የአስተዳደሩን የመሰረታዊ ድርጅትና የህዋስ አመራር አካላት በፓርቲ አደረጃጀትና የአሰራር መመሪያዎች ላይ በቂ ግንዛቤ ይዞ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
7. በከተማው/አስተዳደሩ ለኢንቨስትመንት እና ለመካከለኛና አነስተኛ የማምረትና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት መስፋፋት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የስራ እድል ማስፋት፣ የከተማው መልካም አስተዳደር ችግርን መፍታት፣ የከተማው የመኖሪያ እጥረት መቅረፍና በከተማ መሬት አስተዳደር አፈፃፀምና ሌሎች ተግባራት ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡
8. ተጠሪነታቸው አዲስ አበባ ድሬደዋ ለስራ አስፈፃሚና ለፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ሲሆን የተቀሩት ተጠሪ ለሆኑለት መዋቅር አስተባባሪ ኮሚቴ እና ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 32. የከተማ/የአስተዳደሩ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር፣

1. አስተባባሪ ኮሚቴው ሳምንታዊ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ በመደበኛ ስብሰባው የሚከተሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይወያያል፡፡
   ሀ) በሳምንቱ ውስጥ በከተማው/በአስተዳደሩ የተከናወኑ የመንግስትና የፓርቲ ስራዎች የነበሩትን ዋና ዋና እንቅስቃሴዎች አስመላክቶ አጠር ያለ ግምገማ ያደርጋል፡፡
   ለ) ከሚቀርቡት ሪፖርቶች በመነሳት በመንግስት ስራዎችና የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎች ሊኖር የሚገባውን ቅንጅት በሚመለከትና አስፈላጊ ሆነው የተገኙ ውሳኔዎች ይሰጣል፣
   ሐ) የሳምንቱ ሪፖርት መነሻ በማድረግ አስፈላጊ ውሳኔዎች ያስተላልፋል፣
   መ) በሳምንት የሚፈፀሙ እቅዶችና በቀጣይ ሳምንት ትኩረት የሚሰጣቸው አቅጣጫዎች ይቀይሳል፡፡
2. የወር፣ የሩብ አመትና አመታዊ ግምገማዎችን ያካሂዳል ግብረ መልስ ይሰጣል የቀጣይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡
3. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
4. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 33. የከተማ/የአስተዳደሩ ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ

የከተማው/የአስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1. የፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ..........................................................................ሰብሳቢ
2. የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ............................................................................አባል
3. የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ .......................................................................አባል
4. የህዝብ ግንኙነት ዘርፍ ኃላፊ ..................................................................አባል
5. በፓርቲ ጽ/ቤት ቋሚ ሆነው የሚሰሩ የወጣቶችና ሴቶች ሊግ ኃላፊዎች ያለድምጽ ..........................................................................................................አባል
6. የፓርቲው ጽ/ቤት ኃላፊ እንደአስፈላጊነቱ በአመራር ኮሚቴዉ እያስወሰነ ሌሎች የስራ ኃላፊዎችን ሊጨምር ይችላል፡፡

## አንቀጽ 34. የከተማው/የአስተዳደሩ ፓርቲ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የፓርቲው ጽ/ቤት በመተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የከተማው የፖለቲካ፣ የአደረጃጀትና የህዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡ ፡
2. ከበላይ አካል የሚወርዱ እቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ከተማ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚውን አካል ኦረንቴሽን ሰጥቶ ያሰማራል፣ የስራውን አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይመራል፣
3. መሰረታዊ ድርጅቶችና ህዋሳት በአደረጃጀታቸው ጠንካራና ተልዕኮ ፈፃሚ ሆነው እንዲወጡ የሚያስችል ድጋፍና አመራር መስጠትና ፖለቲካዊ ግንዛቤያቸውን እንዲዳብር ይሰራል፡፡
4. በከተማው/በአስተዳደሩ የሚካሄደውን የልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራዎች ከመተግበር አኳያ ያሉ መልካም ልምዶችን እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡

5. የፓርቲው የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በከተማው/በአስተዳደሩ በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል ያስፈፅማል፣ ይገመግማል፣ ይፈጽማል፣
6. በከተማው/በአስተዳደሩ ውስጥ በሚገኙ የአባላት ማህደር፣ መረጃ የፓርቲ ሰነዶች የፓርቲውን ገንዘብና ንብረት በበላይነት ያስተዳድራል፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
7. ፓርቲው በህብረተሰቡ ዘንድ ያለው ተቀባይነት እንዲጨምርና ህብረተሰቡ በአቋሞቻችን ዙሪያ መግባባት እንዲፈጥር ያደርጋል፡፡
8. የወጣትና ሴቶች ሊጎች አደረጃጀት በማጠናከር ሰፊ አመራር መሰረት እንዲጣል ያደርጋል፡፡
9. በከተማው/በአስተዳደሩ ከሚገኙ ህጋዊና ሰላማዊ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ የውድድር ባህል እንዲዳብር ይሰራል፡፡ የፓርቲያችንን አቋሞች በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ትግል ተቀባይነት እንዲያገኙ ጥረት ያደርጋል።
10. የመሰረታዊ ድርጅትና የህዋስ አመራር አቅም ግንባታ ስራዎች ያሉበትን ደረጃና ችግሮች ይገመግማል፣ የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡
11. ተጠሪነታቸው አዲስ አበባ እና ድሬደዋ ለከተማ/ለአስተዳደሩ አስተባባሪ ኮሚቴና ለብልጽግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ይሆናል፡፡ የተቀሩት ለክልል ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል።

## አንቀጽ 35. የከተማው/የአስተዳደሩ ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. የፓርቲው ጽ/ቤት ሳምንታዊ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡
4. በሳምንቱ በከተማው/በአስተዳደሩ የፖለቲካዊና የአደረጃጀት ስራዎች የነበሩትን ዋና ዋና እንቅስቃሴዎች አስመልክቶ አጠር ያለ ግምገማ ያደርጋል፡፡ አቅጣጫም ያስቀምጣል፡፡

## አንቀጽ 36. የአዲስ አበባ ክፍለ ከተማ የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የከተማ ብልጽግና ፓርቲ አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1. የክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ ................................................ሰብሳቢ
2. ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚ ......................................................አባል
3. የፓርቲው ጽ/ቤት ኃላፊ .................................................ም/ሰብሳቢ
4. የፖለቲካ ኃላፊ ..........................................................................አባል
5. የአደረጃጀት ኃላፊ ....................................................................አባል

## አንቀጽ 37. የክፍለ ከተማ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፣

1. ከከተማ የፓርቲው አስተባባሪ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የክፍለ ከተማውን የፖለቲካ ስራና የመንግስት ስራዎች እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይመራል፣
2. የከተማ ፓርቲው አስተባባሪ ያወጣውን እቅድ አፈፃፀም ስራን ተከታትሎ ያስፈፅማል፣ ይፈፅማል
3. የፓርቲና የመንግስት ስራዎች ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣
4. በየወረዳ ሆኑ በሌሎች ክፍለ ከተማ የተገኙ መልካም ልምዶችን በመቀመር እንዲሰፋ ያደርጋል፣
5. በክፍለ ከተማ የሚካሄዱ የፓርቲና የመንግስት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይከታተላል፣ ይመራል፣
6. በክፍለ ከተማ ያሉትን የፓርቲና የመንግስት አመራር አካላትን ፖለቲካዊ ብቃት በመገንባት ተልእኳቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ የማብቃት ስራ ይሰራል፡፡
7. የወረዳ የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴና ካቢኔ አባላት ምደባ የውሳኔ ሃሳብ ቀጥሎ ላለው የፓርቲ ጽ/ቤት ያቀርባሉ፣ ሲፀድቅ ያሰማራሉ፣
8. የክፍለ ከተማ የመዋቅር የህዝብ፣ የተፎካካሪ ሃይሎች ሁኔታን በዝርዝር በማወቅ እየገመገመ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፡፡
9. ስለ ስራው ክንውን ቀጥሎ ላለው የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፣ የመልካም ልምዶችን የማስፋት ስራው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይገመግማል፡፡ ለችግሮችም የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

10. የመንግስትና ፓርቲ ስራዎች በተገቢው መንገድ ተቀናጅተው እየተሰሩ መሆናቸውን ይገመግማል፡፡
11. የፓርቲው የአሰራርና አደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይገመግማል፡፡
12. ተጠሪነቱ ለከተማው ፓርቲው አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 38. የክፍለ ከተማ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 39. የክፍለ ከተማ የፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የክፍለ ከተማ ፓርቲ አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል

1. የፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ..........................................................................ሰብሳቢ
2. የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ .......................................................................ም/ሰብሳቢ
3. የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ......................................................................አባል
4. የህዝብ ግንኙነት ዘርፍ ኃላፊ ..................................................................አባል
5. የክፍለ ከተማ ሁለቱ ሊጎች ያለ ድምጽ ይሳተፋሉ፡፡

## አንቀጽ 40. የክፍለ ከተማ ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የክፍለ ከተማ የፖለቲካ፣ የአደረጃጀትና የህዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፣
2. ከከተማ ፓርቲ ጽ/ቤት የሚወርዱ እቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ክፍለ ከተማ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፣ ያሰማራል በስራው ሂደትም ተከታትሎ ይደግፋል፡፡

3. በክፍለ ከተማ የሚካሄደውን የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና የፖለቲካዊና ፓርቲ ስራዎች ከመተግበር አኳያ ያሉ መልካም ልምዶችን በመለየት በመቀመር እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡
4. የአባላት የእለት ተእለት ግንባታ ስራን እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ ጠንካራ የህዋስና መሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል፣ ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፣
5. በፓርቲው የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር የስልጠና ስራ ያጠናል፣ ያቅዳል፣ ያደራጃል ስልጠናውም እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡
6. በከተማው ፓርቲው ጽ/ቤት በሚሰጡ አቅጣጫ መሰረት የፓርቲውን ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የስራ አፈፃፀም እና እቅዶች በሚዲያና በህዝብ ግንኙነት መሳሪያዎች ለህዝብ ያስተዋውቃሉ፣
7. የክፍለ ከተማው አባላት፣ አመራር፣ ህዝብ እና የተፎካካሪ ኃይሎች ሁኔታን በየጊዜው እየተከታተለ ተገቢው የማስተካከያ አቅጣጫ እየሰጠ ይሄዳል፡፡
8. በብልጽግና መጽሄት ላይ ተመስርቶ ለሚካሄደው የአባላት አቅም ግንባታ ስራን ያስፈፅማል፣
9. በየሩብ አመት ወረዳዎችን ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ በአካል በመውረድ ያያል፣ ይገመግማል ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ናሙናው የሚመረጠው ጠንካራ፣ መካከለኛና ደካማ የተባሉትን በመምረጥ የሚፈፀም ይሆናል፡፡
10. ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማ አስተባባሪ ኮሚቴና ለከተማ ፓርቲ ኮሚቴ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 41. የክፍለ ከተማ ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡
4. የወረዳ አመራርን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፣
   ሀ) በየሩብ አመቱ ከወረዳ ፓርቲ አመራር ኮሚቴ ጋር የስራ ግምገማ ያደርጋል፡፡

ለ) በየወሩ ከወረዳ አመራር ጋር የአፈፃፀም ደረጃ የፅሁፍ ሪፖርት ተቀብሎ ተገቢውን ግብረ መልስና ድጋፍ ይሰጣል፡፡

ሐ) በየሳምንቱ ከወረዳ ጋር የስልክ ልውውጥ በማድረግ ኢንፎርሜሽን ይቀበላል

መ) አመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማና የቀጣይ አመት እቅድ ለወረዳ ፓርቲ አመራር ኦረንቴሽን ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 42. የአዲስ አበባ ከተማ የወረዳ/ድሬደዋ ቀበሌ የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የከተማ ብልጽግና ፓርቲ አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1. የወረዳ/የቀበሌ ዋና ስራ አስፈፃሚ .................................................ሰብሳቢ
2. ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚ .............................................................አባል
3. የፓርቲው ጽ/ቤት ኃላፊ ..........................................................ም/ሰብሳቢ
4. የፖለቲካ ኃላፊ ..........................................................................አባል
5. የአደረጃጀት ኃላፊ .......................................................................አባል

## አንቀጽ 43. የአዲስ አበባ ከተማ የወረዳ/የድሬደዋ ቀበሌ የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊ

1. የፖለቲካ ስራና የመንግስት ስራዎች የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይመራል፣
2. የበላይ አካል ያወጣውን እቅድ አፈፃፀም ስራን ተከታትሎ ማስፈፀም፣
3. የፓርቲና የመንግስት ስራዎች ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣
4. በወረዳ/በቀበሌ የሚካሄዱ የፓርቲና የመንግስት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይከታተላል፣ ይመራል፣
5. የፓርቲና የመንግስት አመራር አካላትን ፖለቲካዊ ብቃት በመገንባት ተልእኳቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ የማብቃት ስራ ይሰራል፡፡
6. የወረዳ/ቀበሌ የመዋቅር፣ የህዝብ፣ የተፎካካሪ ሃይሎችን ሁኔታን በዝርዝር በማወቅ እየገመገመ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፡፡

7. ስለ ስራው ክንውን ቀጥሎ ላለው የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
8. የመንግስትና ፓርቲ ስራዎች በተገቢው መንገድ ተቀናጅተው እየተሰሩ መሆናቸውን ይገመግማል፡፡
9. ተጠሪነቱ አዲስ አበባ ለክፍለ ከተማ እና ድሬደዋ ለአስተዳደሩ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 44. የአዲስ አበባ ከተማ የወረዳ/የድሬደዋ አስተዳደር ቀበሌ የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር፣

1. የፓርቲው ጽ/ቤት ሳምንታዊ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡
2. ምልአተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።

## አንቀጽ 45. የወረዳ/ቀበሌ የፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ  አደረጃጀት፣

የወረዳ/የቀበሌ ፓርቲ አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1. የፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ..............................................................................ሰብሳቢ
2. የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ..........................................................................ም/ሰብሳቢ
3. የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ........................................................................አባል
4. የህዝብ ግንኙነት ዘርፍ ኃላፊ ..................................................................አባል
5. ሁለቱ ሊጎች ያለ ድምጽ ይሳተፋሉ፡፡

## አንቀጽ 46. የወረዳ/ቀበሌ ፓርቲ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የፖለቲካ፣ የአደረጃጀትና የህዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ከክፍለ ከተማ/ከአስተዳደሩ የሚወርዱ እቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ወረዳ/ቀበሌ ክላስተር ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፣ ያሰማራል በስራው ሂደትም ተከታትሎ ይደግፋል፣

3. በወረዳው/ቀበሌ የሚካሄደውን የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና የፖለቲካዊና ፓርቲ ስራዎች ከመተግበር አኳያ ያሉ መልካም ልምዶችን በመለየትና በመቀመር እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡
4. የአባላት የእለት ተእለት ግንባታ ስራን እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ ጠንካራ የህዋስና የመሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል ተግባራዊ መሆኑም ያረጋግጣል፡፡
5. በፓርቲው የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር የስልጠና ስራ ያጠናል፣ ያቅዳል፣ ያደራጃል ስልጠናውም እንዲካሄድ ያደርጋል፣
6. የስራ አፈፃፀም እና እቅዶች በሚዲያና በህዝብ ግንኙነት መሳሪያዎች ለህዝብ ያስተዋውቃሉ፡፡
7. የወረዳ/የቀበሌ መዋቅር፤ ሕዝብ የተፎካካሪ ኃይሎች ሁኔታን በየጊዜው እየተከታተለ ተገቢው የማስተካከያ አቅጣጫ እየሰጠ ይሄዳል፡፡
8. በብልፅግና መጽሔት ላይ የሚካሄደው የአባላት የአቅም ግንባታ ስራዎችን ይመራል፣
9. ተጠሪነቱ ለወረዳ/ለቀበሌ አስተባባሪ ኮሚቴ እና ክፍለ ከተማ/አስተዳደሩ ፓርቲ ኮሚቴ ጽ/ቤት ይሆናል፣

## አንቀጽ 47. የወረዳ/የቀበሌ ፓርቲ አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. የፓርቲው ጽ/ቤት ሳምንታዊ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡
2. ምልዓተ ጉባዔው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምጽ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምጽ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡
4. መሰረታዊ ድርጅቶችና ህዋሳትን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ መስጠት።
   ሀ. በየሩብ አመቱ የስራ ግምገማ ያደርጋል፡፡
   ለ. በየወሩ መሰረታዊ ድርጅቶችና ህዋሳት ያሉበት አፈፃፀም ደረጃ የፅሁፍ ሪፖርት ተቀብሎ ተገቢውን ግብረ-መልስና ድጋፍ ይሰጣል፡፡
   ሐ. የሩብ ዓመት ተግባራት ይገመግማል፡፡

መ. አመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማና ቀጣይ አመት ዕቅድ ለሚመለከታቸው አካላት ኦሬንቴሽን ይሰጣል፡፡

# ክፍል አምስት

# ለዞን/ለወረዳ/ልዩ ወረዳ ተጠሪ የሆኑ ከተሞች አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር

## አንቀጽ 48. የከተማ አመራር አካላት አደረጃጀት

የከተማ አመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ

1. የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ
2. የፓርቲ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ

## አንቀጽ 49. የከተማ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት

የከተማ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል

1. ከንቲባ ................................ ሰብሳቢ
2. ም/ከንቲባ ........................... አባል
3. ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ .............. ም/ሰብሳቢ
4. የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ............ አባል
5. የአረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ......... አባል

## አንቀጽ 50. የከተማ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. ከዞን/ከወረዳ/ልዩ ወረዳ አስተባባሪ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የከተማውን የፖለቲካ ስራና የመንግስት ስራዎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይመራል፣
2. የፓርቲና የመንግስት ስራዎች ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣
3. በከተማው የሚካሄዱ የፓርቲና የመንግስት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይከታተላል፣ ይመራል፣ እንዲሁም በስሩ ያሉትን የቀበሌ አመራር አካላትን በቅርብ ይደግፋል፡፡

4. በየደረጃው ያሉትን የፓርቲና የመንግስት አመራር አካላትን ፖለቲካዊ ብቃት በመገንባት ተልዕኮአቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ ስራ ይሰራል፡፡
5. የከተማ የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴና ካቢኔ አባላት ምደባ የውሳኔ ሐሳብ ቀጥሎ ላለው የፓርቲ ጽ/ቤት ያቀርባሉ፤ ሲጸድቅ ያሰማራሉ፤ የቀበሌ አስተባባሪ ኮሚቴና ካቢኔ አባላት ምደባ ያፀድቃል፡፡
6. ከፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የወጡ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ይፈፅማል፣
7. በከተማው መዋቅር፣ የሕዝብ፣ የተፎካካሪ ፖርቲዎች ሁኔታን በዝርዝር እየገመገመ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፣
8. ተጠሪነቱ ለዞን/ለወረዳ/ለልዩ ወረዳ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 51. የከተማ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. አስተባባሪ ኮሚቴው ሳምንታዊ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ በመደበኛ ስብሰባዎች የሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይወያያል፣
   ሀ) በሳምንቱ ውስጥ በከተማው የተከናወኑ የመንግስትና የፓርቲ ስራዎች የነበሩትን ዋና ዋና እንቅስቃሴዎች አስመልክቶ አጠር ያለ ግምገማ ያደርጋል፣
   ለ) ከሚቀርቡት ሪፖርቶች በመነሳት በመንግስት ስራዎችና የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎች ሊኖር የሚገባውን ቅንጅት በሚመለከትና አስፈላጊ ሆነው የተገኙ ውሳኔዎች ይሰጣል፣
   ሐ) የሳምንቱ ሪፖርት መነሻ በማድረግ አስፈላጊ ውሳኔዎች ያስተላልፋል፣
   መ) በሳምንት የሚፈፀሙ ዕቅዶችና በቀጣይ ሳምንት ትኩረት የሚሰጣቸው አቅጣጫዎች ይቀይሳል፣
2. የወር፣ የሩብ አመትና አመታዊ ግምገማዎችን ያካሂዳል ግብረ-መልስ ይሰጣል የቀጣይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
3. ምልዓተ ጉባዔው 50+1 ነው፡፡
4. ውሳኔዎች በተባበረ ድምፅ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 52. የከተማ ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት

የከተማ/የወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ አባላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ .................. ሰብሳቢ
2. የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ .................. ም/ሰብሳቢ
3. የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ............... አባል
4. በፓርቲ ጽ/ቤት ቋሚ ሆነው የሚሰሩ የወጣቶችና ሴቶች ሊግ ኃላፊዎች ያለድምጽ አባል
5. የፓርቲው ጽ/ቤት ኃላፊ እንደአስፈላጊነቱ በአመራር ኮሚቴ አስወስኖ ሌሎች የስራ ሃላፊዎችን ሊጨምር ይችላል።

## አንቀጽ 53. የከተማ ፓርቲ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የፓርቲው ጽ/ቤት በመተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የወረዳው የፖለቲካዊ፣ የአደረጃጀትና የሕዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ከዞን/ከወረዳ/ልዩ ወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት የሚወርዱ ዕቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚውን አካል ኦረንቴሽን ሰጥቶ ያሰማራል፡፡ የስራውን አፈፃፀም ይከታተላል ይመራል፡፡
3. የፓርቲ አደረጃጀት አመራርና አባላት በስራቸው ግምባር ቀደም እንዲሆኑ ፖለቲካዊ ግንዛቤያቸው እንዲዳብር ያደርጋል፡፡
4. በከተማው የሚካሄደውን የልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራዎች ከመተግበር አኳያ ያሉ መልካም ልምዶችን እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡
5. የአባላት የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራን በተቀመጠው አቅጣጫ እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ ጠንካራ የህዋስና መሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራችንን ያቅዳል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል ይመራል፡፡
6. በወረዳው የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር ስልጠና፣ ሴሚናር፣ የመ/ድርጅቶች ኮንፈረንስ ያስተባብራል፣ ይመራል፡፡

7. የፓርቲው የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል ያስፈፅማል፣ ይፈፅማል፣
8. በከተማ ውስጥ በሚገኙ የአባላት ማህደር፣ መረጃ፣ የፓርቲ ሰነዶችና የፓርቲውን ገንዘብና ንብረት በበላይነት ያስተዳድራል፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
9. የከተማ ሕዝብ፣ የተፎካካሪ ፓርቲዎች እና አፍራሽ ኃይሎች ሁኔታን በየጊዜው እየተከታተለ ተገቢው የማስተካከያ አቅጣጫ እየሰጠ ይሄዳል፡፡
10. የአመራሩን የስነ-ምግባርና የመፈፀም ብቃት በማዳበር ብቃት ያለው አመራር በበቂ ቁጥር እንዲፈጠሩ በትኩረት ይሰራል፣
11. በልሳናትና በራሪ ጽሑፎች እንዲሁም በብልፅግና መጽሔት ላይ ለሚካሄደው የአባላት ግንባታ ከዞን ፓርቲ ጽ/ቤት የሚተላለፉትን ከወረዳ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ያደርጋል፣
12. ተጠሪነቱ ለከተማ አስተባባሪ ኮሚቴ፣ ለዞን/ለወረዳ/ልዩ ወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 54. የከተማ ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፡፡
2. ምልዓተ ጉባዔው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

# ክፍል ስድስት

## የቀበሌ አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር

### አንቀጽ 55. የቀበሌ አመራር አካላት አደረጃጀት

የቀበሌ አመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ
2. የፓርቲ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ

### አንቀጽ 56. የቀበሌ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት

የቀበሌ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የቀበሌ አስተዳዳሪ ..................... ሰብሳቢ
2. የቀበሌ ም/አስተዳዳሪ ................. አባል
3. የቀበሌ ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ........... ም/ሰብሳቢ
4. የቀበሌ ስራ አስኪያጅ ................. አባል
5. የቀበሌ ወጣቶች ተወካይ ............... አባል
6. የቀበሌ ሴቶች ተወካይ .................. አባል

### አንቀጽ 57. የቀበሌው ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. ከከተማ/ወረዳ/ልዩ ወረዳ አስተባባሪ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የቀበሌውን የፖለቲካ ስራና የመንግስት ስራዎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይመራል፣
2. የፓርቲና የመንግስት ስራዎች ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣ ይገመግማል፣
3. የተገኙ መልካም ልምዶችን በመቀመር በቀበሌው ውስጥ የማስፋት ሥራ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣
4. የሚካሄዱ የፓርቲና የመንግስት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይከታተላል፣ ይመራል፣ እንዲሁም በስሩ ያሉትን የመሰረታዊ ድርጅትና የህዋስ አመራር አካላትን በቅርብ ይደግፋል፡፡

5. የቀበሌ የፓርቲ አስተባባሪ እና ካቢኔ የአመራር ምደባ የውሳኔ ሀሳብ ቀጥሎ ላለው የፓርቲ አስተባባሪ እና ፓርቲ ጽ/ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ያሰማራል፣
6. የቀበሌ መዋቅር፣ የሕዝብ፣ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ሁኔታን በዝርዝር እየገመገመ ለሚመለከተው ክፍል ያሳውቃል፣
7. የፓርቲው የአሰራርና አደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በቀበሌ ውስጥ በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይገመግማል፡፡
8. ተጠሪነቱ ለከተማ/ለወረዳ/ልዩ ወረዳ/ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል

## አንቀጽ 58. የቀበሌ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡
2. ምልዓተ ጉባዔው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 59. የቀበሌ ብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት

የቀበሌ ፓርቲ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ አባላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የቀበሌ ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ………………… ሰብሳቢ
2. የቀበሌ መሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢ ………… ም/ሰብሳቢ መሰረታዊ ድርጅት ሁለትና ከዛ በላይ ከሆነ አባላት ይሆናሉ፣
3. የቀበሌ መሰረታዊ ድርጅት የፖለቲካ ኃላፊ …………. አባል
4. የቀበሌ መሰረታዊ ድርጅት የአደረጃጀት ኃላፊ ……… አባል
5. በፓርቲው የወጣቶችና ሴቶች ሊግ ሰብሳቢዎች ያለድምፅ አባል

## አንቀጽ 60. የቀበሌው ብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የፓርቲው ጽ/ቤት በመተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የቀበሌው የፖለቲካዊ፣ የአደረጃጀትና የሕዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ከከተማ/ወረዳ/ልዩ ወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት የሚወርዱ ዕቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚውን አካል ኦሬንቴሽን ሰጥቶ ያሰማራል፡፡ የስራውን አፈፃፀም ይከታተላል ይመራል፡፡
3. የቀበሌ የፓርቲ አመራርና አባላት በስራቸው ግምባር ቀደም እንዲሆኑ ፖለቲካዊ ግንዛቤያቸው እንዲዳብር ያደርጋል፣
4. በቀበሌ ውስጥ የሚካሄደውን የልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራዎች ከመተግበር አኳያ ያሉ መልካም ልምዶችን እንዲስፋፉ ያደርጋል፣
5. የአባላት የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራን በተቀመጠው አቅጣጫ እየተከናወነ መሆኑንና ጠንካራ የህዋስና መሰረታዊ ድርጅት አመራር ስራን ያቅዳል ተግባራዊነቱንም ይከታተላል ይመራል፡፡
6. በቀበሌው የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር ስልጠና፣ የቀበሌ ኮንፈረንስ ያስተባብራል፣ ይመራል፡፡
7. የፓርቲው የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል ያስፈጽማል፡፡
8. በቀበሌ ውስጥ በሚገኙ የአባላት ማህደር፣ መረጃ፣ የፓርቲ ሰነዶችና የፓርቲውን ገንዘብና ንብረት በበላይነት ያስተዳድራል፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
9. የቀበሌ ሕዝብ፣ የተፎካካሪ ፓርቲዎችና አፍራሽ ኃይሎች ሁኔታን በየጊዜው እየተከታተለ ተገቢው የማስተካከያ ሥራ ይሰራል፣
10. የአመራርን የስነ-ምግባርና የመፈፀም ብቃት በማዳበር ብቃት ያለው አመራር በበቂ ቁጥር እንዲፈጠሩ በትኩረት ይሰራል፣
11. የቀበሌው አመታዊ ዕቅድ መነሻ በማድረግ በየሩብ አመቱ በመዘርዘር ለፈፃሚ አካላት ተገቢውን ኦረንቴሽን ይሰጣል፡፡

12. በዕቅድ አፈፃፀም ሂደት ውስጥ የአፈፃፀም ችግሮች ሲኖሩ አስፈላጊውን ማስተካከያና ድጋፍ ይሰጣል፣
13. በልሳናትና በራሪ ጽሑፎች እንዲሁም በብልፅግና መጽሔት ላይ ለሚካሄደው የአባላት ግንባታ ከከተማ/ወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት የሚተላለፉትን ከቀበሌ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
14. ተጠሪነቱ ለከተማ/ወረዳ/ልዩ ወረዳ አስተባባሪ ኮሚቴና ለፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 61. የቀበሌው ፓርቲ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፡፡
2. ምልዓተ ጉባዔው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምፅ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሰባት

## በየደረጃው የሚኖር የፓርቲ ኮንፈረንስ ውክልና፣

**አንቀፅ 62. በብልፅግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 25 (4) መሰረት በየደረጃው የፓርቲ ኮንፈረንሶች የሚዋቀሩ እንዲሁም በአንቀፅ 26 እና 27 መሰረት ተግባርና ኃላፊነታቸውን የሚከውኑ ሆኖ፤ለዚሁ ተግባራዊነት ኮንፈረንሶቹ በሚከተለው አግባብ በየደረጃው በሚኖር ውክልና ይመሰረታሉ፡-**

1. የክልል፤ የዞን፤ የወረዳ/ልዩ ወረዳ፤ የከተማ እና ቀበሌ የፓርቲ ኮንፈረንሶች ውክልናና ስብጥር በአባላት ብዛት ይወሰናል፤
2. እያንዳንዱ አደረጃጀት የአባላት ብዛትን መሰረት በማድረግ በሚሰጠዉ ኮታ ላይ ተመስርቶ በየአደረጃጀቱ በአባላት ቀጥተኛ ተሳትፎ በሚካሄድ ምርጫ የኮንፈረንስ ተሳታፊዎቹን የሚወክል ይሆናል፣
3. ለክልል ኮንፈረንስ እንደ ክልል አባላት ብዛት ከ300 እስከ 1500 አባላት ይሳተፋሉ፤

4. በዞን/በዞን ደረጃ የሚታዩ ከተሞች ደረጃ እንደ  አባላት ብዛት ከ500 እስከ 1000 አባላት ይሳተፋሉ፤
5. ልዩ ወረዳ 600፤ ወረዳዎቸና ከተሞች እንደ አባላት ብዛት ከ300 እስከ 500 አባላት ይሳተፋሉ፤
6. በቀበሌ ደረጃ እንደ አባሉ ብዛት ከ250 አሰከ 300 ይሳተፋሉ፡፡
7. ዉክልናዉ  ያታዊ ተዋፅኦ በጠበቀ መልኩና ፍትሀዊ መሆን አለበት፤

## ክፍል ስምንት

## የመሰረታዊ ድርጅትና የሕዋሳት አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር

## አንቀጽ 63. የመሰረታዊ ድርጅት አደረጃጀት

1. የመሰረታዊ ድርጅት በክልል፣ በዞን፣ ከተማ፣ ወረዳና በቀበሌ ውስጥ የሚገኙ ሙሉና እጩ አባላትን ያካተቱ ሁለትና ከዛ በላይ የሆኑ ህዋሳትን በመያዝ የሚደራጁ ሆኖ፡-
   ሀ. የመንግስት ሰራተኞች /ለክልል፣ ዞን/ልዩ ወረዳ፣ ከተማ፣ ወረዳና ቀበሌ መስርያቤቶች/ የሚሰሩ የዘርፉ ማለትም የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ አስተዳደራዊ መሰረታዊ ድርጅቶች የሚቋቋሙ ሆኖ፣ ተጠሪነታቸው በየደረጃው ላለ ፓርቲ ጽ/ቤት ወይም ለሚዋቀረው ፓርቲ ኮሚቴ ይሆናል፡፡
   ለ. በየክልሉ ያሉ የፌደራል አባላት በሚሰሩበት ተቋም የሚደራጁ ሆኖ፤ ተጠሪነታቸው ለከተማ ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡
   ሐ. የመምህራን፣ የአስተዳደር ሰራተኞች እና ተማሪዎች መሰረታዊ ድርጅት በተቋም ወይም በወረዳ፣ በቀበሌ የሚደራጅ ሆኖ ተጠሪነቱ ለሚገኝበት ቀበሌ ወይም ወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡
   መ. በሆስፒታል የሚሰሩ አባላት መሰረታዊ ድርጅት በተቋማቸው የሚቋቋም ሆኖ ተጠሪነቱ ለከተማ (አዲስ አበባ ለክ/ከተማ) ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡
   ሠ. የገጠር አርብቶና አርሶ አደሮች አደረጃጀት፣ የገጠር ባለሙያዎች እንዲሁም የወጣቶችና ሴቶች ተወካዮች እና በሌሎች ስራ የተሰማሩትን ባካተተ መልኩ፤ እንደ አባላት ብዛት በቀበሌ፣ በቀጠናና በመንደር በመሰረታዊ ድርጅት ይደራጃሉ። ተጠሪነታቸው ለቀበሌያቸው ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

ረ. የከተማ ነዋሪዎች መሰረታዊ ድርጅቶች በመኖሪያ በቀበሌ/ወረዳ የሚደራጁ ሲሆን፣ ተጠሪነታቸውም ለቀበሌው/ወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

ሰ. በአንድ ዘርፍ የተሰማሩ ወይም አንድ አካባቢ ተደራጅተው የሚሰሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ቁጥራቸው በቂ ከሆነ በአንድ መሰረታዊ ድርጅት ታቅፈው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ቁጥራቸው አነስተኛ ከሆነ ተመሳሳይ ባህርይ ያላቸው በክላስተር ይደራጃሉ፡፡ ተጠሪነታቸው ለየቀበሌያቸው ወይም ወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል።

ሸ. የላብአደሮች መሰረታዊ ድርጅት በሚሰሩባቸው ተቋማት ወይም በኢንዱስትሪ ክላስተር የሚቋቋሙ ሆነው፣ ተጠሪነታቸው ለየቀበሌያቸው/ወረዳ ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

2. በየትኛውም ደረጃ የሚቋቋሙ መሰረታዊ ድርጅት ከ22-210 አባላት ይኖሩታል፡፡ የአባላት ቁጥር ባነሰባቸው አካላት ቁጥራቸው እስከሚጨምር ድረስ ተመሳሳይ ባህሪና የቦታ ቅርበት ያላቸው በአንድ መሰረታዊ ድርጅት መደራጀት ይችላሉ፡፡

3. እያንዳንዱ መሰረታዊ ድርጅት 10-12 አባላት ባሉት የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ ይመራል፡፡ አመራሩም በመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ ይመረጣል፡፡

4. የሚመረጡት የአመራር አባላት የሚከተሉትን መሰረታዊ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. በተሰማራበት የስራ መስክ ባስመዘገበው የስራ ውጤት ለሌሎች አርአያ የሆነ፣

ለ. በሙያውና በስነ-ምግባሩ ምስጉን የሆነና የተሰጠውን ተልዕኮ በብቃት የሚወጣ፣

ሐ. ለውጡን ወደፊት ይዞ የመሄድ ራዕይ ያለው አባል ይሆናል፣

መ.የፓርቲውን አሰራሮች በማወቅና ተግባራዊ በማድረግ የተሻለ እንቅስቃሴ የሚያደርግ፣

ሠ. በተሰማራበት ስራ ሳይወሰን ከዚያ ውጭ በሚደረጉ ሌሎች የልማትና የመልካም አስተዳደር እንቅስቃሴዎች ዙሪያ ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረከተ፣

ረ. በአካባቢው ሕ/ሰብና የስራ ጓደኞቹ ዘንድ በስራውና በማሕበራዊ ግንኙነቱ የተሻለ ተቀባይነት ያተረፈ፣

ሸ. የመሰረታዊ ድርጅቱ አመራር አባላት እስከተቻለ ድረስ ከልዩ ልዩ ህዋሳት አባላት መካከል እንዲመረጡ ይደረጋል፡፡

ቀ. የመሰረታዊ ድርጅቱ አመራር ኮሚቴ የራሱን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ ፀሀፊንና ገንዘብ ያዥ ይመረጣል፡፡ በስሩም የሚከተሉት ንዑሳን ኮሚቴዎች ይኖሩታል፡፡

ሀ. የፖለቲካ ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ

ለ. የአደረጃጀት ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ

ሐ. የፋይናንስ ንኡስ ኮሚቴ

## አንቀፅ 64. የመሰረታዊ ድርጅት ተልእኮ፡-

1. በሚኖሩበት አካባቢ ውስጥ የሚካሄዱትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ጉዳዮች፣ የመልካም አስተዳደርና የሰላም ተግባራት በብቃት እንዲንቀሳቀሱ ማብቃት፡፡
2. የአባላትና የአመራር አካላት ፖለቲካዊና ስነ-ምግባራዊ ብቃት ማጎልበቻ፣ የተሞክሮ መለዋወጫ መድረክ ሆኖ ማገልገል፡፡
3. በልማት፣ በመልካም አስተዳደርና በፖለቲካ ስራዎች ያሉትን መልካም ልምዶች በእያንዳንዱ አባል በተሟላ መልኩ ማስፋፋት፡፡
4. በማያቋርጥ አኳኋን የአዳዲስ አባላት ምልመላ እንዲካሄድ ተገቢውን አመራርና ድጋፍ ይሰጣል፣ አባላት ጠንካራ ፖለቲካዊ ህይወት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

## አንቀፅ 65. የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. በመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ የፀደቀውን ዕቅድ ዝርዝር አፈፃፀም በማዘጋጀት ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣
2. በልማት፣ በመልካም አስተዳደርና በፖለቲካ ስራዎች ያሉትን መልካም ልምዶች በእያንዳንዱ አባልና መዋቅራቸው ደረጃ የማስፋት ስራ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት መከናወኑ ይረጋግጣል፣
3. የህዋስ አመራርን ፖለቲካዊና የአመራር አቅም በሴሚናሮችና በግምገማ ነክ ስልጠናዎች በቀጣይነት የመገንባት ስራ ይሰራል፣
4. የንዑሳን ኮሚቴዎችን እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ አመራር ይሰጣል፣
5. የህዋሳት ውይይት አፈፃፀምን ይከታተላል፡፡ በውይይቱ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በመለየት እንዲሰራበት ያደርጋል፡፡ ፈጣንና ውጤታማ የግብረ መልስ ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣

6. በስሩ የተደራጁ ህዋሳት ጠንካራ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ አስፈላጊውን አመራር ይሰጣል።
7. ከህዋሳት የሚቀርብለትን የእጩ አባላት ሪፖርት መሰረት በማድረግ ሙሉ አባል መሆን የሚገባቸውን ያፀድቃል፡፡
8. አጠቃላይ አባላት ተልእኮአቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይከታተላል፣ በዚህ ረገድ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፡፡
9. በፓርቲው መተዳደርያ ደንብ መሰረት ለመሰረታዊ ድርጅት የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶች ያከናውናል፤፤ መተዳደርያ ደንቡ በሚሰጠው ስልጣን ክልልም የአባላትን ቅጣት ይወስናል፡፡
10. ለመሰረታዊ ድርጅቱ ኮንፈረንስ በየሦስት ወሩ፣ አንድ እርከን ቀጥሎ ላለው ፓርቲ ጽ/ቤት ወይም ለኮሚቴ በየወሩ የተከናወነውን ፖለቲካዊና አደረጃጀት እንቅስቃሴ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
11. የአባላትን ማህደር በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል፡፡
12. ለመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶን ያከናውናል፡፡
13. የአባላት መዋጮ በደረሰኝ ሰብስቦ ለሚመለከተው ክፍል ገቢ ያደርጋል፡፡
14. ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስና በየደረጃው ላለው ፓርቲ ጽ/ቤት ወይም ለሚዋቀረው ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 66. የመሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

1. የመሰረታዊ ድርጅቱን ፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራ ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡
2. የህዋስ አመራር ፖለቲካዊ አቅም ግንባታ ስራን ይከታተላል፣ በበላይነት ይመራል፡፡
3. የጥናት ህዋሳት ጠንካራ የተደራጁ አህዶች ሆነው እየተንቀሳቀሱ መሆናቸው ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡
4. የአመራር ኮሚቴውንና የመሰረታዊ ድርጅቱን ኮንፈረንስና አስቸኳይ ስብሰባዎች በሰብሳቢነት ይመራል፡፡
5. ለስብሰባዎቹ የሚሆን የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ወዘተ… ያዘጋጃል ወይም የሚመለከታቸው ኮሚቴዎች እንዲዘጋጁ በማድረግ ለስብሰባው ያቀርባል፡፡
6. ከበላይ አካል ጋር ኮሚቴውን በመወከል ይገናኛል፡፡ ለበላይ አካል ሪፖርት ያቀርባል። ከበላይ አካል መመሪያ ይቀበላል፡፡

7. ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴና ለየመዋቅራቸው ለፓርቲ ጽ/ቤ ኃላፊን ለኮሚቴ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 67. ምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

1. ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፣
2. የፖለቲካ ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ የተቀመጡ ስራዎችን በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፡፡
3. ከሰብሳቢው የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡
4. ተጠሪነቱ ለሰብሳቢውና ለፖለቲካ ኃላፊ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 68. የፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

1. ለአደረጃጀት ንኡስ ኮሚቴ የተቀመጡ ስራዎችን በበላይነት ይመራል ኮሚቴውን ያስተባብራል፡፡
2. የመሰረታዊ ድርጅቱና የአመራር ኮሚቴዎችን ሰነድ ይይዛል፡፡
3. ከሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡
4. ተጠሪነቱ ለሰብሳቢውና አደረጃጀት ኃላፊ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 69. የፖለቲካ ሥራዎች ንኡስ ኮሚቴ አመራር አባላት አደረጃጀት

1. ንኡስ ኮሚቴው ሦስት የአመራር አባላት ሲኖሩት እነርሱም
   ሀ. የመሰረታዊ ድርጅቱ ምክትል ሰብሳቢ ............................ ሰሰብሳቢ
   ለ. አንድ የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል ............. ም/ሰብሳቢ
   ሐ. አንድ የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል ............ አባል ይሆናሉ፡፡
2. በዚህ ንኡስ ኮሚቴ ውስጥ የአባላት ፖለቲካዊ የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራ፣ የስልጠና፣ ኮንፈረንስ፣ የአባላት ዓቅም ግንባታ ስራ፣ በልሳናትና በብልፅግና መፅሔት ላይ የሚደረግ ውይይት ይመራል፣

## አንቀጽ 70. የንኡስ ኮሚቴው ዋና ዋና ተግባራት

1. የፖለቲካ ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት ይኖሩታል፡፡
   ሀ. እያንዳንዱ አባል ብቁ ፖለቲካዊ ግንዛቤና አቋም ኖሮት ተልእኮዎቹን ለመፈፀም የሚያስችለው ሁኔታ ላይ እንዲገኝ ተከታታይ ውይይትና ተግባር ውስጥ እንዲገባ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣
   ለ. እያንዳንዱ አባልና አመራር መልካም ልምዶችን ለማስፋፋትና ለመተግበር የሚያስችለው የአስተሳሰብ ዝግጁነት እንዲኖረው ይሰራል፣

2. የህዋስና የመሰረታዊ ድርጅት አመራሮች አቅም ግንባታ ስራ እንዲሰራ ያደርጋል፣
   ሀ. የፖለቲካ ስራ ዘርፍ በሚያወጣው እቅድ መሰረት መከናወኑን ይከታተላል፡፡
   ለ. የተገኘውን ውጤትና የሚታዩ ችግሮችን በመከታተል ይገመግማል፣ መፍትሔ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡
3. አባላት በልሳናት በብልፅግና መፅሔት ላይ ውይይት እንዲያካሂዱ ማድረግ፡፡
   ሀ. ለመሰረታዊ ድርጅት አባላት መወያያ የሚሆኑ የልሳናትና በብልፅግና መፅሔት ፅሁፎችን እቅድ ያዘጋጃል፡፡
   ለ. በእቅዱ መሰረት ልሳናት የብልፅግና መፅሔት በወቅቱ የሚመጡበትን ስርዓት ይዘረጋል በዚሁ መሰረት መድረሳቸውን ያረጋግጣል፣
   ሐ. የህዋሳት የውይይት ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ በፕሮግራማቸው መሰረት ውይይት ማካሄዳቸው የከታተላል፡፡
   መ. በህዋሳት ውይይት ላይ የተነሱ ጉዳዮችን ከህዋሳት የፖለቲካ ስራ ሃላፊዎች በመቀበል ምላሽ ይሰጣል፡፡
   ረ. ከንኡስ ኮሚቴው አቅም በላይ የሆነውን ለመሰረታዊ ድርጅት አመራርና ለፖለቲካ ስራ ዘርፍ በማቅረብ አቅጣጫ ይቀበላል፣ ለህዋሳት ያሳውቃል፡፡

4. በመሰረታዊ ድርጅት ደረጃ ኮንፈረንስ እንዲካሄድ በማድረግ አባላት በኮንፈረንስ መድረኮች ላይ ተገኝተው በሚገባ መወያየታቸውንና ግንዛቤ መያዛቸውን ይከታተላል፣
5. የተለያዩ ሴሚናሮች ለአባላት እንዲሰጡ ማድረግ፣

ሀ. የመወያያ ርእሶችንና ሰነዶች በወቅቱ መድረሳቸውን እንዲሁም አወያዮች መሟላታቸውን ይከታተላል፣

ለ. በበላይ አካል በሚሰጠው እቅድ መሰረት አባላት በተሟላ መልኩ በሴሚናሮች ላይ መሳተፋቸውንና በቂ ፖለቲካዊ ግንዛቤ ማዳበራቸውን ይከታተላል፣

6. ስልጠናዎች እንዲሰጡ ማድረግ፡-

ሀ. የሚካሄዱ ስልጠናዎችን ያደራጃል፣

ለ. በበላይ አካል የሚካሄዱ ስልጠናዎች ሲኖሩ የምልመላና የሰው ሃይል ዝግጅት ስራዎችን ያከናውናል፣

ሐ. የተሰጡ ስልጠናዎችን ውጤት ተከታትሎ ይገመግማል፣ ክፍተቶችን ይለያል፣ ሪፖርት ያቀርባል፣

መ. ወደፊት ሊሰጡ ስለሚገባቸው ስልጠናዎች ለከተማና መሰረታዊ ድርጅት አመራር ሃሳብ ያቀርባል፣

7. ከፖለቲካ ኮሚቴ ጋር የስራ ግንኙነት በመፍጠር ድጋፍ ያገኛል፣ ሪፖርትም ያቀርባል። የንኡስ ኮሚቴውን ስራ በተመለከተ ከፖለቲካ ኮሚቴ ጋር እየተገናኘ አስፈላጊውን የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፣ ድጋፍ ያገኛል፣

8. ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢና ለፖለቲካ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 72. የአደረጃጀት ስራዎች የንኡስ ኮሚቴ አደረጃጀትና አሰራር

1. ኮሚቴው ሦስት የአመራር አባላት ሲኖሩት እነሱም፡-

ሀ. የመሰረታዊ ድርጅቱ ፀሀፊ ........................................ ሰብሳቢ

ለ. አንድ የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል .......... ምክትል ሰብሳቢ

ሐ. አንድ የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል .......... አባል ይሆናሉ፡፡

2. የንኡስ ኮሚቴውን መረጃዎችና የአባላትን የግል ማህደር መያዝ፣ የአደረጃጀትና አሰራር መመሪያዎችን ተፈፃሚነት መከታተልና እያንዳንዱ አባል በአደረጃት ታቅዱ ተልዕኮዎቹን እየፈፀመ መሆኑን፣ አዳዲስ የአፈፃፀም ልምዶችን መቀመርና ወደ ሌሎች የማስፋፋት ስራ ይሰራል፡፡

## አንቀጽ 73. የአደረጃጀት ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ ዋና ዋና ተግባራት

የአደረጃጀት ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. አባሉ የተደራጀና ጠንካራ አደረጃጀት ሆኖ ተልዕኮዎቹን የሚወጣ መሆኑን የሚያረጋግጥ ስራ ማቀድና ማከናወን፣
   ሀ. እያንዳንዱ አባል በተለይም የመሰረታዊ ድርጅትና የሕዋስ አመራር በተልዕኮው ላይ ግልፅ የሆነ፣ ፖለቲካዊ ግንዛቤው ከፍ ያለና ጠንካራ አቋም ያለው፣ በተግባር ራሱ ሰርቶና ተጠቅሞ ለሌሎች በአስተማሪነቱ የሚጠቀስ እንዲሆን ያደርጋል፣
   ለ. አባላችን የተደራጀና እንደ አንድ ተልዕኮ ፈፃሚ ኃይል ጠንካራ ተጽዕኖ እያሳረፈና ለውጥ እያመጣ መሆኑን ማረጋገጥ፣
   ሐ. አባሉ ተደራጅቶ ወደ ስራ ለመግባትና የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት ያሉበትን ችግሮች በየጊዜው እየገመገመ የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡
2. የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያዎች በአባላት ታውቀው ስራ ላይ እንዲውሉ የሚያስችል ዲስፕሊን መፍጠር፣
   ሀ. አባላት በአደረጃጀትና አሰራር መመሪያዎች ላይ በቂ ግልጽነት የያዙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ ካልያዙ ስልጠና እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
   ለ. የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያዎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ችግሮች ካሉ ያስተካክላል፡፡
3. የአባላት አደረጃጀት መፍጠርና ማጠናከር
   ሀ. ሁሉም አባላት በመሰረታዊ ድርጅትና በህዋስ አደረጃጀቶች ውስጥ መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፣
   ለ. አደረጃጀቶቹ የአባላትን ግንዛቤ በማሳደግና ተግባራዊ እንቅስቃሴያቸውን በመምራት በኩል ወሳኝ ሚና እንዳላቸው በትክክል እንዲገነዘቡ ያደርጋል፣
   ሐ. አባላት ሚናቸውን እየተጫወቱ መሆናቸውን መከታተልና ማረጋገጥ፣ ለሚታዩ ችግሮችም መፍትሄ ያስፈልጋል፣
4. እያንዳንዱ አባል ተልዕኮዎቹን ስራ ላይ ማዋሉን ክትትል በማድረግ የእያንዳንዱን አባል ደረጃ መለየት፣ ድጋፍ ማድረግ፣
   ሀ. እያንዳንዱ አባል ተልዕኮዎቹን በግልጽ መያዙን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

ለ. በዚሁ መሰረት ስራ ላይ ማዋሉን በጥብቅ ክትትል ይለያል፣

ሐ. በለውጡ አፈፃፀም ውጤቱ ላይ በመመስረት በየጊዜው ለእያንዳንዱ አባል ደረጃ እንዲወጣለት ያደርጋል፣

መ. አባሉ ግንባር ቀደም ሚናውን ስለመወጣቱም በአባላት እንዲመዘንና የማጠናከሪያ ድጋፍ ይሰጣል፣

ሠ. ግንባር ቀደም ሚናቸውን የማይወጡ ካሉ ተገቢውን ማስተካከያ ያደርጋል፣

5. የአባላት ማህደር በየጊዜው እየተሞላ መያዙን ማረጋገጥ

ሀ. እያንዳንዱ አባል የግል ማህደር የተዘጋጀለት መሆኑን ያረጋግጣል፣

ለ. በየ6 ወሩ በሂስና ግለሂስ ላይ የተመሰረተ የታደሰ ማህደር መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፣ የአባሉ የግል ማህደር ለተፈላጊ ስራ እንዲውል ያደርጋል፡፡

6. ከአደረጃጀት ኮሚቴ ጋር የስራ ግንኙነት በመፍጠር ድጋፍ ያገኛል፣ ሪፖርትም ያቀርባል፤ የንኡስ ኮሚቴውን ስራ በተመለከተ ከአደረጃጀት ጋር በየጊዜው እየተገናኘ አስፈላጊውን የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ድጋፍ ያገኛል፣

7. የደጋፊ አደረጃጀቶችን ማደራጀትና ማጠናከር

ሀ. የሊጎችና የማህበራት አደረጃጀቶች እንዲሁም የደጋፊዎች ትስስራዊ አደረጃጀቶች መደራጀታቸውንና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ መግባታቸውን ይከታተላል፣

ለ. ንኡስ ኮሚቴው በየ15 ቀኑ እየተገናኘ ስራውን ይገመግማል

8. ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢና ለአደረጃጀት ኮሚቴ ይሆናል፣

## አንቀጽ 74. የፓርቲው ፋይናንስ ንኡስ ኮሚቴ

1. የንኡስ ኮሚቴው አባላት ቁጥር ሁለት ሆኖ በፓርቲው የገቢ እቅድ ማዘጋጀት፣ ገቢ ማሰባሰብና ማስገባት ዙሪያ የስራ ክፍፍል ይኖራቸዋል፡፡
2. የፓርቲውን አመታዊ ገቢ ዕቅድ ማዘጋጀት እና በእቅዱ መሰረት ማሰባሰብ፣
3. ገቢዎች በህጋዊ ደረሰኝ በመሰብሰብ ለፓርቲ ጽ/ቤት ገቢ ያደርጋል፣
4. የልሳናትና የብልፅግና መፅሔት የመፅሄት ሽያጭ ገቢ ያደርጋል፣
5. ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢና ለፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 75. የመሰረታዊ ድርጅት አሰራር

1. የመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድ ያደርጋል፣
2. የመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ የለውጥ ሂደት ያለበት ደረጃ በቁልፍ አጀንዳነት ተይዞ ይገመገማል፣
3. የኮንፈረንስ ጊዜ ቢያንስ ከ1 ወር በፊት አስቀድሞ እንዲታወቅ ይደረጋል፡፡ በተቻለ መጠን ኮንፈረንሱን ተከታታይ የሆኑ የበአል ቀናትን ግምት ውስጥ በማስገባት እንዲጠራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
4. የመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ በየሶስት ወሩ የሚካሄድ ይሆናል፣
5. የኮንፈረንስ አጀንዳዎች ምን ሊሆኑ እንደሚገባ ተመካክሮ ለጥናት ህዋሳት ማሳወቅና ጥናት ህዋሳት የሚፈልጉት አጀንዳ ካለ እንዲዲጠቀሙ ማድረግ ይኖርበታል፣
6. ልዩ ልዩ ንኡሳን ኮሚቴዎች የስራ አፈፃፀማቸውን በተመለከተ የየራሳቸውን ሪፖርት በአጭሩ እንዲያዘጋጁና በሪፖርቱ የቀጣይ እቅድም መነሻዎች እንዲቀርቡ ይደረጋል።
7. ከበላይ አካል በኮንፈረንሱ ላይ ቢታዩ ይጠቅማሉ የሚባሉ አጀንዳዎችን በመቀበል ከየመዋቅራቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ለውይይት እንዲቀርቡ ይደረጋል፣
8. በኮንፈረንስ መድረክ ላይ አጀንዳዎችን በማፅደቅ በቅደም ተከተል ውይይት ይደረግባቸዋል፣
9. አባላት በየርዕሱ ነፃ ሆነው ሀሳባቸውን እንዲገልፁ፣ እንዲቃወሙም ሆነ እንዲደግፉ ሰፊ እድል መስጠትና በበቂ ሁኔታ ከተወያዩ በኋላ ወደ ውሳኔ ሃሳብ የማምራት አግባብን መከተል ይገባል፣
10. የውሳኔ ሃሳቡ በፅሁፍ ተዘጋጅቶ በንባብ እንዲቀርብና በድምፅ እንዲወሰን ይደረጋል፣
11. በኮንፈረንሱ ማጠቃለያ ላይ የጋራ የአቋም መግለጫ ማውጣት፣ የአቋም መግለጫው ሁሉንም የውሳኔ ሃሳቦች በአጭር በአጭሩ እንዲይዝ በማድረግ ለጥናት ህዋሳት ሃላፊዎች ኮፒ እንዲደርስ ማድረግ ይገባል፣
12. በኮንፈረንሱ ማጠቃለያ ላይ የአመራሩ ሂስና ግለሂስ ሪፖርት ለአባሉ እንዲቀርብና የሚጨመር ወይም የሚስተካከል ካለ እንዲስተካከል ይደረጋል፣
13. የአመራር ምርጫ በየአመቱ መጀመሪያ በሚካሄደው ኮንፈረንስ ይሆናል፣

14.አባላት ወይም የበላይ አካል አስቸኳይ ኮንፈረንስ ሲጠይቁ ለመላ አባላት በጥናት ህዋሳት ስብሰባ ላይ አሳውቆ ግማሽ ያህሉ ከደገፈው እንዲካሄድ ይደረጋል፣

15.የኮንፈረንሱ አጠቃላይ ሂደት በቃለ-ጉባኤ እንዲያዝ ይደረገል፣

16.የኮንፈረንሱ ምልአተ ጉባዔ ከመሰረታዊ ድርጅቱ አባላት ከግማሽ በላይ /50%+1/ ሲገኙ ይሆናል፣

17.ኮንፈረንሱ በድምፅ ብልጫ የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች በኮንፈረንሱ ከተገኙት ውስጥ ከግማሽ በላይ /50%+1/ የደገፉት ሊሆን ይገባል፡፡

## አንቀጽ 76. በኮንፈረንሱ ውሳኔዎች መሰረት ተግባርን መምራት

1. ኮንፈረንሱ ከተጠናቀቀ በኋላ አመራሩና መላ አባላት በየአደረጃጀታቸው አማካይነት ፈጥነው ወደ ስራ መግባትና የተቀመጡትን ተግባራት ለማስፈፀምና ግቡን ለማሳካት መረባረብ ይገባቸዋል፣
2. የጋራ ስራዎችን በስምምነታቸው መሰረት በከፍተኛ የሃላፊነት መንፈስ ይፈፅማሉ፣
3. የመልካም አስተዳደርና ሌሎች ተግባራትን በእቅዱ መሰረት መፈፀም፣
4. ከእያንዳንዱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ብቁ ትምህርት መውሰድ፣ በአመራር ደረጃ ምርጥ የአባላት ልምዶችን እየለቀሙ ለሁሉም ማሳወቅና የአፈፃፀም ስልቶች የጋራ ሃብት እንዲሆኑ ማድረግ፣
5. የስራ አፈፃፀም ሂደቱን በተቀመጡ ጊዜዎች በመደበኛነት መገምገምና አስፈላጊውን የእቅድ ማስተካከያ እያደረጉ ስራውን በጥራት መስፈፀም ይጠበቅባቸዋል፡፡

## አንቀጽ 77. በአመራር ደረጃ የመማማር አሰራርን በጥቅም ላይ ማዋል

1. የአመራሩ የስራ አፈፃፀሙን መሰረት በማድረግ መማማር ፕሮግራም በየወሩ ያካሂዳል፣
2. በየሶስት ወሩ በተራ ቁጥር 1 የደረሰበትን ውጤት ለመሰረታዊ ድርጅት በአጭሩ አቅርቦ ያስገመግማል፡፡ ከአባላት የሚቀርቡ ትችቶች ካሉ ተቀብሎ ምላሽ ይሰጣል፣
3. በሁሉም ደረጃ የሚካሄደው መማማር ፕሮግራም ገንቢና በተጨባጭ ድክመቶች ላይ የተመሰረተ፣ ስራን እንጂ ሰውን ማእከል ያላደረገ እንዲሆን ይደረጋል፣

## አንቀጽ 78. የመሰረታዊ ድርጅት አመራሮች አሰራር

የአመራር ኮሚቴ ስብሰባና ግንኙነት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

1. አመራር ኮሚቴው በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡ በዚህ መሰረት፡-
   ሀ. ከህዋስና ከንዑሳን ኮሚቴ የመጣለትን ሪፖርት፣ እንዲሁም ከበላይ አካል የሚወርድለትን እቅድና አቅጣጫ ላይ ውይይት ያደርጋል፣ ለህዋሳትና ለንዑሳን ኮሚቴ አቅጣጫ ይሰጣል፣
2. እጩ አባላትን ወደ ሙሉ አባልነት የማሸጋገር ውሳኔን ይወስናል፣ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ለህዋስ ያሳውቃል፣
3. አመራር ኮሚቴው በሁሉም ጉዳዮች ላይ ያለውን ሃሳብ ለህዋሳት በአፋጣኝ ያሳውቃል፣

## አንቀጽ 79. የንኡሳን ኮሚቴዎች አሰራር

1. ሁሉም ንዑሳን ኮሚቴዎች በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ይኖራቸዋል፣
2. በስብሰባው ያለፈውን የስራ አፈፃፀም ይገመግማሉ፣ የቀጣይ 15 ቀናት የስራ እቅድ በማፅደቅ ስራዎችን ተከፋፍለው ስምሪት ያደርጋሉ፣
3. ለመሰረታዊ ድርጅት የሚቀርብ ሪፖርት ያዘጋጃሉ፣ ያቀርባሉ፣
4. ለህዋሳት ኮሚቴ አቅጣጫዎችን ያወርዳል፣

## አንቀጽ 80. የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ከፓርቲ ጽ/ቤት ኮሚቴ ጋር የሚኖረው ግንኙነት

1. ሰብሳቢው ከፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ጋር እና ከኮሚቴ ሰብሳቢ ጋር የስራ ግንኙነት ያደርጋል፣
2. የፓርቲ ጽ/ቤት ወይም ኮሚቴ አመራሩ በ3 ወር አንድ ጊዜ የመሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ፣ ፀሀፊና የፋይናንስ ሀላፊ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢዎችን አንድ ላይ ወደ ማእከል በመጥራት የስራ ግምገማ ያደርጋል፡፡ የዚህ ግንኙነት ዝርዝር አተገባበር ስለአመራር የግንኙነት ከላይ በተገለፀውና ውስጥ በሰፈረው አግባብ መሰረት ይፈፀማል፣

3. እንደየአስፈላጊነቱ በየደረጃው ያሉት የፓርቲ ጽ/ቤት ፖለቲካና አደረጃጀት ኃላፊዎች ከመሰረታዊ ድርጅት አመራር አባላት ጋር መደበኛ የስራ ግዚያቸውን በማይጋፋና ለነሱ አመቺ በሆነ ጊዜ የጋራ ስብሰባ ያደርጋሉ፣
4. ከበላይ አካል የሚሰጠውን እቅድና ልዩ ልዩ መመሪያ ቆጥሮ ይቀበላል፡፡ እቅዶችን ለተፈፃሚነት ያዘጋጃል፣
5. ለበላይ አመራር የሚቀርብ ትችት ካለው በዚህ መድረክ በመጠቀም ያቀርባል፣
6. በየሶስት ወሩ የተሟላ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ለፓርቲ ጽ/ቤት ወይም ለኮሚቴ ይልካል፣

## አንቀጽ 81. የህዋሳት አደረጃጀት

1. የመሰረታዊ ድርጅት ለአባላት የዕለት ተዕለት ግንባታ የሚጠቀሙበት የህዋስ አደረጃጀት ይኖራቸዋል፡፡ የህዋስ አባላት ቁጥር ከ11-35 ይሆናል፣
2. ህዋሳት የሚመሰረቱት ሙሉና እጩ አባላትን በመያዝ በመኖሪያ አካባቢ በስራ ቦታ ሆኖ በሚከተለው መልኩ ይሆናል፣
   ሀ. የመንግስት ሰራተኞች /በክልል፣ በዞን፣ በከተማ፣ በወረዳ/ልዩ ወረዳና በቀበሌ መስሪያ ቤቶች/ የሚሰሩ በተቋም ወይም በየዘርፉ ማለትም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አስተዳደራዊ ዘርፎችን መሰረት አድርገው ይደራጃሉ፣
   ለ. በየክልሉ ያሉ የፌደራል ተቋማት አባላት ህዋሳት በሚሰሩባቸው ተቋማት የሚደራጁ ይሆናል፣
   ሐ. የመምህራን፣ አስተዳደር ሰራተኞችና የተማሪዎች ህዋስ አመቺ በሆነበት ቦታ /ተቋም፣ በወረዳ፣ በቀበሌ/ ደረጃ ይደራጃል፣
   መ. የሆስፒታል አባላት እንደ አመቺነቱ በሚሰሩበት ተቋም፣ ወረዳ/ቀበሌ ደረጃ ይደራጃሉ፣
   ረ. የገጠር አርብቶና አርሶ አደሮች ህዋሳት መንደር/ቀጠናን መሰረት በማድረግ ይደራጃሉ፡፡
   ሰ. በገጠር የተሰማሩ የመንግስት ሰራተኞች ህዋሳት የገጠር ባለሙያዎች እና በሌሎች ስራ የተሰማሩትን ባካተተ መልኩ የስራ ቦታ ወይም ቀበሌን መሰረት በማድረግ ይደራጃሉ፡፡

ሸ. የከተማ ነዋሪዎች ህዋሳት የመኖርያ ቦታን መሰረት በማድረግ በቀበሌ፣ በመንደር፣ በቀጠና ወይም በወረዳ ደረጃ ይደራጃሉ፡፡

ቀ. የከተማ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት አባላት በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ የሚደራጁ ሆኖ ቁጥራቸው አነስተኛ ከሆነ በአቅራቢያቸው ካለ ህዋስ ጋር ይደራጃሉ፡፡

በ. የላብአደር አባላት በስራ ቦታቸው በህዋስ ይደራጃሉ፡፡

ነ. በክልል መንግስታት ወይም በህዝብ ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሚገኙ አባላት እንደአመቺነቱ በሚኖሩበት ቀበሌ ወይም በአቅራቢያቸው ባሉ ተቋማት አደረጃጀቶች ውስጥ ታቅፈው በህዋስ ያደራጃሉ፡፡

3. በአንድ ተቋም የሚሰሩ አባላት ቁጥራቸው ከአስራ አንድ በታች ከሆነ ከሌሎች ተቋም ጋር በክላስተር ይደራጃሉ፣
4. ሁሉም አባል በህዋስ ተደራጅቶ መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል በአንድ የስራ ቦታ ወይም መኖሪያ የአባላት ቁጥር ከ35 በላይ ከሆነ ሌላ ህዋስ መደራጀት ይቻላል፣
5. እያንዳንዱ ህዋስ የራሱን አመራር ኮሚቴ ይመርጣል እነዚህም፡-

   ሀ. ሰብሳቢ

   ለ. የፖለቲካ ኃላፊ

   ሐ. የአደረጃጀት ኃላፊ

   መ. ገንዘብ ያዥ ይሆናሉ
6. ለህዋስ አመራርነት የሚመረጡ አባላት የሚያሟሉት መመዘኛ ከላይ ለመሰረታዊ ድርጅት አመራርነት የሚመረጡ በደረጃው ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች ተመሳሳይ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 82. የህዋስ ተልእኮ

1. አባላት በቀበሌያቸው/በወረዳቸው በመስርያቤታቸው ውስጥ በሚካሄዱ ብልፅግናን የሚያረጋግጡና የሰላም ተግባራት ግንባር ቀደም ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ማብቃት በዚህ ሂደትም አባላትን በተግባር እንዲገነባ ይደረጋል፣
2. በህዋሱ ውስጥ የታቀፉትን አባላት በሙሉ በየግላቸው የሚያዘጋጁትን የግል እቅድ ማፅደቅ፣ አፈፃፀሙን መከታተል፣ መደገፍና ውጤቱን መገምገም፣
3. የአባላትን የፖለቲካዊና ድርጅታዊ ብቃት እንዲኖራቸው ይሰራል፣

4. አዳዲስ አባላት ምልመላ ማካሄድ፣ አባላት በተደራጀ ፓርቲ ህይወት እንዲኖራቸውና የተደራጀ ጠንካራ እንቅስቃሴ እንዲኖራቸው ይደረጋል፣

## አንቀጽ 83. የህዋስ አሰራር

ህዋሶች የሚከተለው ውስጣዊ አሰራር ይኖረዋል

1. በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፣
2. የፖለቲካ ውይይት እና እያንዳንዱ አባል ብልፅግናን በሚያረጋግጡ ዙሪያ በግንባር ቀደምነት የሚያደርገው እንቅስቃሴ፣ የአባላትና ደጋፊዎች የጋራ አደረጃጀት፣ በአጠቃላይም የአባላት እንቅስቃሴ የሚገመገምበት ይሆናል፣
3. በግምገማው ላይ በመመስረትም የመማማር ፕሮግራም እንዲካሄድ ይደረጋል፣
4. የህዋስ ስብሰባ የሚካሄደው ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ይሆናል፣
5. ማንኛውም አባል በህዋስ ስብሰባ የመገኘት ግዴታ አለበት፣ አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ምክንያት የማይገኝ አባል አስቀድሞ የህዋሱን ሰብሳቢ ማሳወቅና ማስፈቀድ ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 84. የህዋሳት እንዲሁም የአመራር ኮሚቴና አባላት ተግባርና ኃላፊነት

1. የህዋስ አመራር ኮሚቴ የሚከተለው ተግባራት ይኖረዋል፡፡
   ሀ. የህዋሱን ሰብሳቢና ሌሎች ኃላፊዎች ይመርጣል፣
   ለ. የህዋስ አባላት በተግባርና በአስተሳሰብ ግንባር ቀደም ሆነው በመንቀሳቀስ ላይ መሆናቸውን ይከታተላል፣
   ሐ. ከመሰረታዊ ድርጅት የመጡ መመሪያዎችን የህዋሱ አባላት እንዲያውቋቸውና በአግባቡ እንዲፈፅሟቸው ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውንም ይቆጣጠራል፣
   መ. አባላት ተልእኮቻቸውን ከመፈፀም አኳያ ያሉበትን ሁኔታ ይገመግማል፣ እያንዳንዱን አባል ዕቅድ በመገምገም ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ውጤቱን ይገመግማል፣
   ሠ. አዳዲስ እጩ አባላት መስፈርቱን አሟልተው መመልመላቸውን ያረጋግጣል፣ እጩ አባልነትን እንዲፀድቅ የውሳኔ ሀሳብ ለመሰረታዊ ድርጅት ያቀርባል፣

ረ. የህዋሱን የውይይትና የግምገማ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ በህዋሱ በማፅደቅም ስራ ላይ ይውላል፣

ሰ. የእጩ አባልነት ጊዜያቸው የሞላ አባላትን ሁኔታ ገምግሞ ወደ ሙሉ አባልነት ሊሸጋገሩ ይገባል ብሎ ያመነባቸውን ሙሉ አባልነታቸው እንዲፀድቅላቸው ለመሰረታዊ ድርጅት ሪፖርት ያቀርባል፣

ሸ. የህዋሱ የውይይት ፕሮግራም ሳይስተጓጎል የሚካሄድበትን ሁኔታ ለመፍጠር ትኩረት ሰጥቶ ይንቀሳቀሳል፡፡ የሌሎችን ህዋሳት መልካም ተሞክሮ በመቅሰም ህዋሱ እንዲጠቀምበት ያደርጋል፣

ቀ. አመራር ኮሚቴው በየ15 ቀኑ መደበኛ ስብሰባ በማድረግ መረጃዎችን ይለዋወጣል፣

በ. ለመሰረታዊ ድርጅት በየወሩ ሪፖርት ይልካል፣

2. የህዋስ ሰብሳቢ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

ሀ. የህዋሱን ስብሰባ በሰብሳቢነት ይመራል፣

ለ. የህዋሱን ፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራ በበላይነት ያስተባብራል፣

ሐ. ህዋሱን በመወከል ከመሰረታዊ ድርጅት አመራር ጋር ይገናኛል፣

መ. ህዋሱ ጠንካራ የተደራጀ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ የሚያስችል አመራር ይሰጣል፣

ሠ. እያንዳንዱን የህዋስ አባል ፖለቲካዊ እንቅስቃሴውን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት ድጋፍ እንዲያገኝ ያደርጋል፣

3. የህዋስ ፖለቲካ ኃላፊ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

ሀ. የአባላትን ፖለቲካዊ ዝንባሌ ተከታትሎ በማወቅና ሪፖርት በማድረግ ተገቢውን ፖለቲካዊ ዝንባሌ ተከታትሎ በማወቅና ሪፖርት በመደረግ

4. የአደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

ሀ. ህዋሷ ጠንካራ ሆና እንድትንቀሳቀስ የሚያስችል አመራር ይሰጣል፣

ለ. እያንዳዱ አባል በአደረጃጀትና አሰራር መመሪያዎች ላይ ያለውን ግንዛቤ ማጎልበትና በስራ ላይ እንዲያውል ይከታተላል፣ አመራር ይሰጣል፣

ሐ. የህዋሱን አባላት ማህደር ይይዛል፣ ሲያስፈልግም ለመሰረታዊ ድርጅቱ ያስተላልፋል፣

መ. የአባላት የመማማር ሂደት ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፣ የየወቅቱን በእያንዳንዱ አባል ማህደር ያሰፍራል፣

ሠ. ህዋሱ እጩ አባል እንዲሆኑ የተቀበላቸውን አባላት ግንባታ ይከታተላል፣ ሙሉ አባል መሆን የሚገባቸውን በወቅቱ በህዋሱ እንዲገመገሙና ሪፖርቱ ለመሰረታዊ ድርጅት እንዲላክ ያደርጋል፡፡ ከመሰረታዊ ድርጅቱ የመጣውንም ምላሽ ህዋሱ እንዲያውቀው ያደርጋል፣

ረ. የህዋሱ አባላት በአባላትና በደጋፊ የጋራ አደረጃጀት አማካኝነት የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ይከታተላል፣

ሰ. ለመሰረታዊ ድርጅት አደረጃት ኃላፊ በየወሩ ሪፖርት ያቀርባል፣

ሸ. ተጠሪነቱ ለህዋሱ ሰብሳቢና ለመሰረታዊ ድርጅቱ የአደረጃት ኃላፊ ይሆናል፡፡

5. የህዋስ ገንዘብ ያዥ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

ሀ. የአባላትን መዋጮ ያቅዳል፣ በህጋዊ ደረሰኝ በማሰባሰብ ለመሰረታዊ ድርጅት ገቢ ያደርጋል፣

ለ. የልሳናትና የብልፅግና መፅሔት ሽያጭ ገንዘብ በማሰባሰብ ገቢ ያደርጋል፣

ሐ. ሌሎች የፓርቲ ደጋፊ ገቢዎችን እንደአስፈላጊነቱ አሰባስቦ ገቢ ያደርጋል፣

መ. ተጠሪነቱ ለህዋስ ሰብሳቢና ለመሰረታዊ ድርጅት ፋይናንስ ኃላፊ ይሆናል፣

## አንቀጽ 85. የደጋፊዎች ቡድን አደረጃጀት

1. እያንዳንዱ የፓርቲ አባል በተሰማራበት የስራ መስክ ይሁን መኖሪያ ቦታ በጋራ አብረው ለሚኖሩና ለሚሰሩ አካላት የፓርቲንና የመንግስት ዓላማዎችና እንቅስቃሴ የማስረዳት ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡
2. በዚህ መሰረት እያንዳንዱ አባል በስራ እና መኖሪያ ቦታው ፓርቲዉን በእዉቀት፣ በገንዘብና በጉልበት  መደገፍ የሚፈልጉ ፈቃደኛ ደጋፊዎች የማፍራትና የጋራ አደረጃጀት ፈጥሮ የመንቀሳቀስ ኃላፊነት አለው፣
3. ከመኖሪያ ቤቱና መስሪያቤቱ ውጪ በደጋፊነት ለመደራጀት ፈቃደኛ የሆነ ሰው ካገኘም ደጋፊው በሚኖርበት ወይም በሚሰራበት አካባቢ ለሚገኝ ህዋስ ስሙ እንዲተላለፍና በአካባቢው እንዲደራጅ የማድረግ ኃላፊነት ይኖረዋል፣
4. እያንዳንዱ ደጋፊ ለመሆን ፍቃደኝነቱን ያረጋገጠ ግለሰብ ከሚቀራረቡትና ከሚስማሙት ሰዎች ጋር እንዲደራጅ ይደረጋል፣
5. የደጋፊዎች ቡድን በተደራጁ የደጋፊዉ ቡድን አባላት በተመረጠ፣ ተቀባይነትና የተግባር መሪነቱ የተረጋገጠ መሪ የሚመራ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 86. የደጋፊዎች ቡድን ተልዕኮ

1. የፓርቲው ደጋፊዎች ቡድን አዳዲስና አስፈላጊ የሆኑ ሀሳቦችን የሚያገኙበት መድረክ ሆኖ ያገለግላል፣
2. የፓርቲው ደጋፊዎች ለፓርቲው ሊያቀርቡ የሚፈልጓቸዉ ጉዳዮች፣ አስተያየቶች፣ መስተካከል ያለባቸዉ አመላከከቶችና አሰራሮች፣ ለፓርቲው የሚያቀርቡት ገንቢ ሐሳቦችና ነቀፌታዎች፣ ሲኖሩ የሚያመቻች መድረክ ሆኖ ያገለግላል፣
3. ፓርቲው ከጠቅላላ ህዝብና ምሁራን ጋር የሚኖረዉን ግንኙነት የሚያስተሳስር መድረክ ሆኖ ያገለግላል፣
4. በሂደትና በሙሉ ፈቃዳቸዉ ወደ ፓርቲው የሚቀላቀሉ አዳዲስ አባላት በተለይ ደግሞ ምሁራን፣ ባለሀብቶች ወጣቶችና ሴቶች የዕጩ አባላት መመልመያ መድረክ ሆኖም ያገለግላል፣
5. ፓርቲው የሚያስፈልገው የእዉቀት፣ ጉልበትና የገንዘብ ድጋፍ ተጨማሪ አቅም ሆኖ ያገለግላል፡፡

## አንቀጽ 87. የአባላትና ደጋፊዎች ቡድን አሰራር

1. የደጋፊዎች ቡድን ከተመሰረተ በኋላ የስብሰባና የውይይት ጊዜ፣ ከፓርቲው ያለው ግንኙነት፣ ሌሎችም የሚመለከት አሰራር ራሱ ይወስናል፣
2. የአባላትና ደጋፊዎች ቡድን በፍላጎትና መግባባት የሚመሰርት ይሆናል፣
3. የደጋፊዎች ቡድን አባላት የፓርቲው አባል መሆን በሚፈልጉበት ጊዜ ጥያቄያቸው በቀጥታ በአቅራቢያቸው ለሚገኝ ህዋስ ያቀርባሉ፡፡ ህዋሱ ያለው ውሳኔ ይገልፅላቸዋል፣
4. በእያንዳንዱ ህዋስ ስር የተደራጁ የደጋፊ አባላት ዝርዝር ማህደራቸው በመሰረታዊ ድርጅት የአደረጃጀት ኃላፊ ይቀመጣል፡፡ በየጊዜው ይታደሳል፣
5. የደጋፊዎች ቡድን አባላት አስተያየታቸው ለሚመለከተው አመራር ይሁን ለኮንፈረንስ መላክ ሲፈልጉ በአቅራቢያቸዉ ላለ የፓርቲ መዋቅር ወይንም እንደአስፈላጊነቱ ይመለከተዋል ብለዉ ለሚያምኑት የፓርቲ መዋቅር ማቅረብ ይችላሉ፣

6. የዴጋፊዎች ቡድን በተስማሙበት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ስለቡድናቸው የስራ አፈፃፀም ነፃ ሁነው ይወያያሉ፡፡ የዉይይታቸዉን ውጤት በአቅራቢያቸዉ ላለና ለሚደግፉቸዉ የፓርቲ መዋቅር እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 88. ውህደቱን በሁሉም የፓርቲ መዋቅሮች በአደረጃጀት ተግባራዊ ለማድረግ የሚኖር አደረጃጀቶች

1. በየክልሉ ከውህደት በፊት የነበሩ የሶስቱ የግንባሩ አባል ድርጅት የነበሩ አዴፓ፣ ኦዴፓ፣ ደኢህዴን እና የአጋር ድርጅት መዋቅሮች ውህደቱ ከተፈፀመ በኋላ ህጋዊ ህልውናቸው ስለተቋረጠ በየክልሉ የነበሩ አደረጃጀቶቻቸው በየሚገኙባቸው ክልሎች በየደረጃዉ ባሉ የብልፅግና ፓርቲ አደረጃጀቶች ታቅፈው የሚንቀሳቀሱ ይሆናል፡፡
2. በተራ ቁጥር አንድ በተጠቀሰው መሰረት በክልል ደረጃ ያሉ አደረጃጀቶች በክልሉ የብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት ባለው አደረጃጀት ውስጥ የሚታቀፉ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ በዞን፣ በወረዳ፣ በከተማ፣ በቀበሌ፣ በመሰረታዊ ድርጅት እና በህዋስ ደረጃ ያሉ አደረጃቶችች በክልሉ ባሉ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማ፣ የቀበሌ የመሰረታዊ ድርጅቶች እና ህዋሳት ውስጥ ታቅፈው የሚደራጁና የሚንቀሳቀሱ ይሆናል፡፡
3. በተራ ቁጥር ሁለት የተጠቀሰውን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ቀደም ሲል የተደራጁት በመኖሪያ ቦታ የነበረ ከሆነ በሚኖሩበት አካባቢ ባሉ አደረጃጀቶች እንዲታቀፉ ይደረጋል፡፡ አደረጃቶቹ በሥራ ቦታ የተደራጁ ከነበሩ በሚሰሩበት ተቋም ባሉ አደረጃቶች ውስጥ ታቅፈው እንዲደራጁና እንዲንቀሳቀሱ ይደረጋል፡፡ ባሉበት መኖሪያ ቦታ ወይም የሥራ ቦታ የብልፅግና ፓርቲ አደረጃጀት ከሌለ በሚቀርባቸው ቦታ እና ተቋም ታቅፈው እንዲደራጁና እንዲንቀሳቀሱ ይደረጋል፡፡
4. ከተራ ቁጥር 1-3 የተዘረዘሩትን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት በተለይ ደግሞ በየአደረጃጀቶቹ የሚካሄደዉን ግንባታ ዉጤታማ ለማድረግ የቋንቋዎች አጠቃቀም ወሳኝ ነዉ፡፡ በመሆኑም በህዋሳትና መሰራታዊ ድርጅቶች በሚካሄዱ ዉይይቶች እና በተለያዩ ደረጃዎች በሚዘጋጁ ስልጠናዎች የሰነድ ዝግጅትና ዉይይቶቹ የሚመሩበት አግባብ በፓርቲወ መተዳደሪያ ደንብ የተቀመጠዉን ተግባራዊ በሚያደርግና የቋንቋዎችን ብዝሀነት በአግባቡ ግምት ዉስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባዋል፡፡

5. በየክልሉ የነበሩ የፌደራል ተቋማት የፓርቲው አባላት በሚሰሩበት ክልል/ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ተደራጅተው ይንቀሳቀሳሉ፣
6. የወጣትና ሴት ሊጎች የፓርቲ አደረጃጀት ተከትሎ በህጋዊ መንገድ ውህደት እስኪፈጥሩ ድረስ ተግባሮችን በጋራ እየሰሩ የጋራ አመራር እየተሰጣቸው በነበረው አደረጃጀት እየተንቀሳቀሱ እንዲቀጥሉ ይደረጋ፡፡
7. የፌዴራል ተቋማት/ የፓርላማ ፤የፌዴራል እና ውጭ ጉዳይ /ዞኖች አደረጃጀት በተመለከተ የፌዴራል ዞን አደረጃጀቱ ቀደም ሲል በተደራጀው 20 ወረዳ ሆኖ በመ/ድርጅትና በሕዋስ እንዲደራጅ ይደረጋል፤ የውጭ ጉዳይ ዞን አደረጃጀቱ በሚኒስቴር መ/ቤቱና በኤምባሲ ደረጃ በወረዳ ፤ በሕዋስና በመ/ድርጀት የሚደራጅ ይሆናል፡፡ ፓርላማ ራሱን ችሎ በመ/ድርጅትና በህዋስ እንዲሁም አንድ ወረዳ ሆኖ ይደራጃል፡፡ ሶስቱንም የፌዴራል ተቋማት  የሚመራና ተጠሪነቱ ለፓርቲው ጽ/ቤት የሆነ የፌዴራል ተቋማት የፓርቲው አሰተባባሪ ኮሚቴ 9 አባላት በማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አሰፈጻሚ ደረጃ ያሉ አመራሮች ይመደባሉ፡፡
8. በክልል ደረጃ የክልል ሴክተር በሶስት ክላስተር ማለትም በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና አስተዳደራዊ ይደራጃል፡፡ በየክላስተሩ 5/5 የፖለቲካ አመራሮች ይኖራሉ፡፡ በየክላስተሩ በቋሚነት ሁለት ሁለት አመራሮችን በመመደብ የዕለት ተዕለት የክትትልና ድጋፍ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፖለቲካ አመራር የሚሰጡ የክልል ሴክተር የፓርቲው አመራር ኮሚቴ 9 አባላት ከከፍተኛ አመራር ይመደባል፡፡ ተጠሪነቱ ለክልሉ ፓርቲው ጽ/ቤት እንዲሆን ይደረጋል፡፡
9. አዲስ አበባና ድሬዳዋ የከተማ /አስተዳደሩ ሴክተር ለአመራር እንዲመች በሶስት ክላሰተር ማለትም በኢኮኖሚ፤በማህበራዊና አስተዳደራዊ በሚል ይደራጃል፡፡ ክላሰተሩን የሚመሩ 5 አባላት ያሉት ኮሚቴ ይኖራል፡፡ሁሉም ሴክተር የሚመሩ ደግሞ 7 አባላት ኮሚቴ ተዋቀሮ ተጠሪነቱ ለከተማው/ለአስተዳሩ ፓርቲ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡ በየክላስተሩ የዕለት ተዕለት የክትትልና ድጋፍ ስራ የሚያከናውኑ ሁለት ሁለት አመራሮችን በቋሚነት በመመደብ  እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡
10. ከአዲስ አበባ ውጭ ክፍለ ከተማ ያላቸው ከተሞች ለዞን/ለወረዳ/ለልዩ ወረዳ ተጠሪ የሆኑ ከተሞች በሚል የተቀመጠው እንደደረጃቸው የሚያገለግል ሲሆን ድሬዳዋ የገጠር ክላስተር ወረዳ የሚለው ይጠቀማል፡፡

የካቲት 2012 ዓ.ም